# ቅዱስ ደል

## መንፈሳዊ ድራማ

# ገፀ ባህሪያት

1.ጌታነህ፡-የእልልታ ባለቤት
2.እልልታ፡-የጌታነህ ባለቤት
3.ሽብሬ፡-የነ አቶ ጌታነህ የቤት ሰራተኛ
4.እሳቱ፡-የጌታነህ ጓደኛ
5.ዶ/ር አለሙ ፡-የጌታነህ ጓደኛ
6.አንዳርጌ(ግርማ)፡- የነ አቶ ጌታነህ ዘበኛ
7.1ኛ እና ሁለተኛ ፖሊስ

# ቅዱስ ድል መንፈሳዊ ድራማ

## ክፍል አንድ

ስልክ፣ኮመዲኖ፣ቁምሳጥን፣እንደሁም ጥሩ ጥሩ እቃዎች የያዘ የሃብታም ሰው ቤት ይታያል፡፡የተጣደ ጀበና ከስኒዎች ጋር ቀራርቦ ይቀመጣል፡፡ሽብሬ ቤት እያስተካከለች ትታያለች፡፡እሳቱ ትልቅ ዶሴ/ፋይል/ ይዞ ወንበር ላይ ተቀምጧል፡፡ በሁለቱ ጭቅጭቅ ተውኔቱ ይጀመራል፡፡

<u>**እሳቱ**</u>:-ሂጂ ወዲያ ምን ትላለች ይቺ ማነው በፍቅር ምሰሶነት የቆመውን የዚህን ቤት ትዳር ለማፍረስ የሚጥረው፡፡

<u>**ሽብሬ**</u>:-እሱን ተወው«ጥሬን ለኛ ብስሉን ለደገኛ»አለ ያገሬ ሰው ሂድና የምታታልለውን አታል ይልቁንም ከጋሽዬ ጋር ሱክ ሱክ እያልክ ፀረ ትዳር የሆነውን የነገር ጦርህን አትስበቅ፡፡

<u>**እሳቱ**</u>:-ኧረ ተይ ሽብሬ ኋላ በምን ተጎዳሁ እንዳትይ፡፡ አጨብጫቢ አንቺስ ከጓዳ ከሴትየዋ ስር ተወትፈሽ የምትፈተፍችው የነገር ፍትፍት ምን ይባላል፡፡

<u>**ሽብሬ**</u>:-ብቻ ነግሬሃለሁ በሁለቱ ባልና ሚስቶች መካከል ለዘመናት ፀንቶ የቆየውን ፍቅር በማርገብ በፅኑ ቃልኪዳን የታሠረውን ትዳር ከወዲያ ወዲህ ባታናጋው ጥሩ ነው፡፡

<u>**እሳቱ**</u>:-አፈኛ ድንቄም እንዲህ አድርጎ አዛኝ የለም«አዛኝ ቅቤ አንጓች»አሉ፡፡አሁን አንቺ ለሴትዋ የሌለ ወሬ ፈጥረሽ ነግረሻት ሴትየዋን ስታስጨንቂያት አላገኘሁሽም ቀጣፊ ሌባ፡፡

<u>**ሽብሬ**</u>:-ስማ አንተ የራሱን ስራ በሰው ላይ የሚያላክክ አይነ ደረቅ ሌባ ማለት አንተ እንጂ እኔ ሽብሬ ሥራዬም አይደለም፡፡

<u>**እሳቱ**</u>:-ማነው ሌባ(ሊመታት ሲነሳ መጥረጊያ አንስታ)

<u>**ሽብሬ**</u>:-ዋ ሰውዬው እንዳትዋረድ(ወደ መቀመጫው ተመልሶ ይቀመጣል ከጥቂት ቆይታ በኋላ)

<u>**እሳቱ**</u>:-እኔምለው አሁን ጭቅጭቅን እንተውና እንዴት ናቸው አሁን ይስማማሉ ?ከዚህ ቤት ከጠፋሁ ይሄው 3ኛ ቀኔ ነው፡፡ ማለቴ በነዚህ ሦስት ቀናት አልተኮራረፉም፡፡

<u>**ሽብሬ**</u>:-አዎን ደህና ናቸው፡፡ግብ ፍቅራቸው እንደ ድሮው አይደለም፡፡አንዳንድ ምቀኞች በመካከላቸው ሳይገቡ አይቀርም/የጎሪጥ ታየዋለች/

<u>**እሳቱ**</u>:-/ወደ እሷ እያፈጠጠ/እውነትም አንዳንድ የእርጎ ዝንቦች ሳይፈለጉ ጥልቅ ሳይሉ አይቀሩም/ጥቂት ፋታ/ አሁን የት ሄደው ነው?

<u>**ሽብሬ**</u>:-በጠዋት ወደ ቤተ ክርስቲያን ነው የሄዱት፡፡ብዙ ቆዩ አሁን ስንት ሰአት ነው?

<u>**እሳቱ**</u>:-/ሠዓቱን አይቶ/ 3:30 ነው፡፡

<u>**ሽብሬ**</u>:-እኔ እምለው አንተ ጋሼ ዓለሙን የት ነው የምታውቃቸው?እዚህ ጋሼ ጋር ሲመጡ ነው ወይስ ሌላ ቦታ ትተዋወቃላችሁ?

<u>**እሳቱ**</u>:-/እንደረሳው በመምሰል/የቱ አለሙ?

<u>**ሽብሬ**</u>:-የጋሼ ጓደኛ ዶክተሩ ናቸዋ

<u>**እሳቱ**</u>:-አ!አስታወስኩት የለም ከጌታነህ ከተዋወቅን በኋላ ነው ያወቅኩት እንጂ ከዚህ በፊትስ አላውቀውም፡፡እንዲያው ጥሎብኝ አልወደውም፡፡ሁሌ እኔን የሚያየኝ በግራ አይኑ ነው፡፡

<u>**ሽብሬ**</u>:-(በአሽሙር)ድሮስ ጥሩ ሰው መች ይወድልህና/ጥቂት ፋታ/ አይ እሱስ እውነትህን ነው፡፡እኔም እንዳንተው ነኝ፡፡ በዚህ ሰሞን ደግሞ ከዚህ ቤት አይጠፉም ጋሼም አልፎ አልፎ በጥርጣሬ ያዩታል፡፡

<u>**እሳቱ**</u>:-እውነትሽን ነው

<u>**ሽብሬ**</u>:-እውነቴን ነው/ጓዳ ትገባለች/

<u>**እሳቱ**</u>:-ተመስገን ነዋ! ዓላማዬም ጅማሪዬም ሀ ብሎ ግብ እየመታ ነው፡፡እሱ ያስጀመረ ያስፈጽመን እንጂ/ጥቂት ፋታ/ ግን ይቺን እሳት እንዴት ነው የማደርገው?ቆይ በፀባይ ነው መያዝ ያለብኝ፡፡ /እያወራ እያለ እነ አቶ ጌታነህ ተከታትለው ይገባሉ/

<u>**ጌታነህ**</u>:- ወይ አቶ እሳቱ ብቻህን ማውራት ጀመርክ፡፡ለማንኛውም ደህና አደርክ

<u>**እልልታ**</u>:-ደህና አደርክ

<u>**እሳቱ**</u>:-/በመደናገጥ የውሸት መልስ በማሰብ/ደህና እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ምን እባክህ ለቀጨኔ ወዳ ፍርድ ቤት መቅረብ ያለበት የሞግዚትነትና የወራሽነት ደብዳቤ ረቂቅ በወረቀት አስፍሬ መጀመሪያ በቃል ልዝለቀው ብዬ ነው፡፡

<u>**ጌታነህ**</u>:-አይ አንተ በቃ እድሜ ልክህን ከፍርድ ቤት አካባቢ አልጠፋም አልክ፡፡ይቺ ሪፖርት መጻፍ፣አልፎ አልፎም ቴምብር መሸጥ ሳታዋጣህ አትቀርም፡፡ለመሆኑ ደህና ነህ ምነው ይሄን ሦስት ቀን ከቤት ጠፋህ?

<u>**እልልታ**</u>:-ከማታምነው ቤት ስትጠፋ ምን ሆኖ ነው ብለን ነበር፡፡

<u>**እሳቱ**</u>:-አለሁ ደህና ነኝ ሰሞኑን ትንሽ ወደ ኢሚግሬሽን አካባቢ ብቅ ብዬ ለጉዞ አመልካቾች ስጽፍ ነበር፡፡ምን እባክህ ራፖርት ጸሐፊው ከባለ ጉዳዩ እጅግ በዝቷል፡፡ደግሞም ገንዘብ ለማግኘት እንጂ የጸሐፊነት ልምድ እንኳን የላቸውም፡፡ እናም እንደኔ አይነት ልምድ ያለው ጸሐፊ ያስፈልግን ነበርና ወደዚያ ሄጄ ነው የጠፋሁት፡፡አንቺስ እንዴት ነሽ ወ/ሮ እልልታ?

**እልልታ**:-አለሁ ደህና ነኝ ፈጣሪ ይመስገን ምነው ባለፈው እድር እከፍልልሻለሁ ብለህ አስጠብቀኸኝ ጠፋህ?

**እሳቱ**:-(ጌታነህን ሰርቆ እያየ)አይ ወ/ሮ እልልታ የኛ ስራ ጸባይ እንደ ዶክተሮች ነው፡፡ዶክተሮች በሽተኛ በላይ፣በላይ እየተከታተለ እንደሚመጣባቸው ሁሉ የኛም የፍርድ ቤት ጉዳይ እንዲሁ ነው፡፡በስራ ምክንያት ቀልቤ ጠፍቶብኝ መች አስታወስኩት ብለሽ ነው፡፡እኔ እምልሽ አቶ ዓለሙ ደህና ነው?

**እልልታ**:-ምን እኔን ትጠይቀኛለህ?አብሮት ውሎ የሚያመሸው ጓደኛው እያለልህ የሱን ጤንነት ከሱ በላይ አውቃለሁ ብለህ ነው?/ሽብሬ ቡና እያፈላች ነበር እንደ መሳቅ እያለች ወደ ጓዳ ትገባለች/

**እሳቱ**:-የለም እንደባለፈው የሚመጣ ከሆነ አንቺም ስለ ጤንነቱ ሳታውቂ አትቀሪም ከሚል እምነት በመነጨ መንፈስ እንጂ በክፋት አስቤው አይደለም፡፡

**እልልታ**:-ለነገሩ ቢመላለስም ጓደኛውን ብሎ ነው እንጂ ለክፋት ነው አላልኩም፡፡

**ሽብሬ**:-/የእጅ ውሃ ይዛ ትመጣለች፡፡ሊታስታጥብ ስትል/

**ጌታነህ**:-አይ ተይው ከቤተ ክርስቲያን ስንመለስ የእልልታ ጓደኛ ፋናዬ አግኝታን እቤቷ ጥሩ ቁርስ ጋብዛናለች፡፡

**እልልታ**:-እውነቱን ነው እንሺው

**እሳቱ**:-አሃ ለዚህ ነዋ ከረፈደ የመጣችሁት

**ጌታነህ**:-ለእሳቱ አቅርቢለት

እሳቱ:-የለም በፊት ከቡናዋ ልቅመስ

**ጌታነህ**:-ይህ ደግሞ የምን ካሜራ ነው?እንደ ፎቶ አንሺም ይቃጣሃል፡፡

**እሳቱ**:-በጨለማ ፍላሽ ስለሌለው ማንሳት ቢያስቸግርም በቀን ግን ያነሳል፡፡ቅድም የሆነ ወዳጄ እቤቴ በተኛሁበት ካሜራውንና  ገንዘቡን ይዞ መጥቶ ፊልም አስሞላልኝ  ብሎኝ ፊልም አስሞልቼለት እየመጣሁ ነው፡፡ ካሜራዋ ግን እንዴት አይነት ካሜራ መሰለችህ፡፡

**ጌታነህ**:-እስቲ አምጣት/ይቀበለዋል ተቀብሎ እያገላበጠ ይመለከታታል/ግሩም ነች ፡፡ኖር ሰላም መጣህ አረፍ በል፡፡

**ዓለሙ**:-ደህና/ዝምታ ይሰፍናል ሽብሬ የቡና ቁርሱንና ቡናውን ታቀርባለች ቡናውን ጠጥተው ሲጨርሱ አቶ ዓለሙ እራሱን እያነቃነቀ እንደ መሳቅ ይላል/፡፡

**ጌታነህ**:-ምነው ምን ሆንክ ብቻህን ትስቃለህ የሚይስቅ ነገር ካለ ይፋ አድርገውና እኛም የሳቁ በረከት ይድረሰን፡፡

**ዓለሙ**:-ስለገረመኝ ነው የሳቅኩት/ከኪሱ አጠር  ያለች ፓምፐሌት እያወጣ/ይገርማል ቅድም ወደዚህ ለመምጣት መንገድ ከመጀመሬ በፊት ፒያሳ ጋር ቆሜ ጫማዬን ሳስጠረግ የህዎ ምስክሮች ነን ባዮች መጥተው ስለ ዓምላክ መንግስት አንዳንድ ነገሮች ሲያወሩ እኔም በጥሞና ካዳመጥኳቸው በኋላ እኔ የራሴ እምነት እንዳለኝ እየነገርኳቸው ሳለ የሆኑ ወጣቶች መጡ  ወዲያውኑ ይቺን  የኔን ነፍስ ለመቀራመት ይሰዳደቡ ጀመር፡፡

**ጌታነህ**:-ጥሩ ነው ቢያንስ የራስህ እምነት እንዳለህ መመስከርህ ጥሩ ነው፡፡እሺ ከዚያስ እንዴት ለቀቁህ፡፡

**ዓለሙ**:-ከዚያ እኔ እንዲያውም የነሱን ጭቅጭቅ ማዳመጡን ያዝኩኝ ለካ ጆቫዎች misunedersatanedinge አለባቸው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሚካኤል ነው ብለው ያምናሉ፡፡እኔን የገረመኝ የነሱ ስብከት አጀማመር ይሄውም ከተመለከትኳቸው ተላላፊ መንገደኞች አንዱ በሽተኛ ስለነበር በሽታ ከስር መሰረቱ እንዴት እንደመጣ በአዳም ጥፋት ምክንያት እንደሆነ እያይዘው መጀመራቸው ሲሆን ሌላው እነሱን ተከትለው የመጡት የኛው የኦርቶዶክስ አማኞች ተሰባኪውን ህዝብ ከነዚህ ነጣቂ ተኩላዎች የሚያድኑበት ስልት ስለደነቀኝ ነው፡፡

**እልልታ**:-አሁንማ ክብር ምስጋና ለፈጣሪ ይሁንና ወጣቶቻችን በእምነት ጥንካሬአቸውም ሆነ በመንፈሳዊ አገልግሎታቸው ከመልካም ዛፍ መፍራት የሚገባውን እውነተኛ የሃይማኖት ፍሬ አፍርተው ዘር እየዘሩ ነው ተመስገን ነው፡፡

**ጌታነህ**:-ልክ ነው ጥንት አባቶቻችን ተተኪ ለማፍራት ካላቸው ቅንአት ሊሆን ይችላል በአውደ ምህረት ማስተማሩን ዘንግተውት ነበር፡፡ ማለት በልብህ አምነህ በአፍህ ብትመሰክር ትድናለህ የሚለውን አባባል ወደ ጎን በመተው ወጣቱን ዳዊት በማስደገም ገድል በማስነበብና የተለያዩ አዋልድ መፃህፍትን በማስተማር ላይ ነበር የሚያተኩሩት አሁን ግን ወጣቱ እራሱ በአግዚአብሔር ቸርነት መንፈሳዊ ምስክርነቱን በመስጠት ላይ ነው፡፡በተለይ(2) ለዚህ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተው 10 ሰዓት የሚሰጠው የአውደ ምህረት  ትምህርት መጠናከር ይመስለኛል፡፡

**እሳቱ**:-/ፋይሎቹን እያገላበጠ/አልተሰሳትከም እንዲያውም በቀደም ከአውራጃ ፍርድ ቤት ቁልቁም በልደታ ወደ ሜክሲኮ ሳቀና  ልደታ ቤተ  ክርስቲያን ሰው ግጥም ብሎ ሞልቷል እኔም ጠጋ ብዬ ምን እንደሆነ ብጠይቅ ትምህርት ነው አሉኝ አልተሳሳትክም፡፡

**እልልታ**:-ግን እኮ የገድል፣ የአዋልደ መፃህፍትና የዳዊት ማስደገሙ ትምህርት ጥሩ ነበር፡፡ነገር ግን ወጣቱን በክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር  በማነጽ ህይወት የሚለውጥ ትምህርት በስፋት በመስጠት  ላይ ከፍተኛ ጥረት ቢደረግ ዛሬ እንደሆነው ጆቫ ዊትነስን የመሳሰሉ የእምነት ፀር መንፍቃን  በአገራችን ዞር ባላሉም ነበር፡፡

**ጌታነህ**:-ለመሆኑ ምንድን ነው የያዝከው
**ዓለሙ**:-እነሱ የሰጡኝን ነው እንካ አንብበው ::አቤት አፋቸው እንዴት ምላጭ መሰለህ በአንዳንድ አባባላቸው ተማኬ ነበር:: ሆኖም እነዚህ ሰንበት ተማሪዎች መጥተው ስማ የኛ ወንድም አንተ የምታምን ነህ የሚያምን ደግሞ ከማያምን ጋር ምንም ህብረት የለውም እነዚህ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፍጡር ነው ከማለት አልፈው ቅዱስ ሚካኤል ነው የሚሉና መፅሐፍ ቅዱስን እንደራሳቸው ፍላጎት የሚቀያይሩ ናቸው አሉኝ::
**እሳቱ**:-እሰይ እንዲህ ነው ምስክርነት::
**እልልታ**:-ደግ አደረጉ
**ዓለሙ**:-እኔም ሚካኤል ነው የሚለው አባባላቸው ገርሞኝ ሳለ «እናንተ እኛ በምንመጣበት መንገድ ለምን ትከተላላችሁ እናንተ ስለተከተላችሁ የሕዮዋ ቃል እንደሁ ከመሰበኩ አይቀርም አለ አንዱ የጀሻ ልጅ ወዲያ ው አንዱ የኦርቶዶክስ ጀግና ብትፈልጉ ከእኛ ጋር በፈለጋችሁት ጊዜ መነጋገር እንችላለን ሌላውን ህዝብ አታሳስቱ እናንተ የተሳሳታችሁት አይበቃም በማለት ተናገረ በዚያው አንድ አንድ ሲባባሉ ሰው ተሰበሰበ ወዲው ጀሻዎች ላይ ጨኸቱ በረከተ እነርሱም ደንግጠው ከአካባቢው ጠፉ እልሃለሁ::
**እልልታ**:-እኔ እንደማስበው በአሁኑ ሰዓት ወጣቱ በቤተ ክርስቲያን ያለው ተሳትፎ እየጎላ በመምጣቱ ለወደፊቱ ለቤተ ክርስቲያንጥሩ ተተኪዎች ይፈራሉ::እኔንም ቢሆን ከልጅነቴ አስተምራ ለሥርዓተ ተክሊልና ለሥጋ ወደሙ ጋብቻ እንድበቃ ያደረገችኝ ሰ/ት/ቤቴ ነች::
**ዓለሙ**:-አይ ከአሁን በኋላስ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ እጀምራለሁ በእርግጥ ፍላጎት ነበረኝ ግን የሚያነሳሳ ሃይል አልነበረኝም :: ለወደፊት እያነበብኩ የሚነሳ ጥያቄ ሲኖረኝ አንቺ ትረጂኛለሽ ወ/ሮ እልልታ አይመስልሽም ?እውቀት እንደሆነ የውበትሽን ያክል ነው የታደልሽው::/ እሳቱ የውሸት ሳል በጣም ይስላል ወዲያው/
**ሽብሬ**:-/ብድግ ብላ በመነሳት/ምነው ምን ሆንክ ውሃ ልስጥህ?
**ጌታነህ**:-ምነው ምን ሆንክ
**እሳቱ**:-ትንታ ቢጤ አለችብኝ አንዳንዴ ነገር ሲሸተኝ ትነሳብኛለች
**ጌታነህ**:-ታዲያ ዶክተሮች እንደሆኑ በእጃችን ናቸው::ሄደህ አትመረመርም/ስልክ ይደወላል ጌታነህ ሄዶ ያነሳና
**ጌታነህ**:-ሄሎ ----ታዲያስ ደህና ነህ ወይ የኔ ጌታ-------ምን? እውነትህን ነው!(በመደንገጥ) የካሳሁን እናት ደከመዋል? እሡስ ልክ ነህ ቆራቢ ናቸው ግን ቢሆንም ለልጃቸው ሲል ቢያተርፋቸው ምናለ ለማንኛውም መጣን ቻው::
**እልልታ**:-ወይ ምስኪን በሽታው እንዲህ ሃይለኛ ነበር እንዴ?
**ዓለሙ**:-እሡስ seriouse case ነበር::
**ጌታነህ**:-(በመነሳት)በል እንሂድ እንጂ እንዲያውም ቆየን
**ዓለሙ**:-እኔ እንኳን እዛ አልሄድም
**ጌታነህ**:-ታዲያ ከእኔ ጋር ካልሄድክ ትንሽ ቆይና ተጫወት
**ዓለሙ**:-የለም ቢያንስ እየሸኘሁህ የምነግርህ ነገር አለኝ
**ጌታነህ**:-ነው!ጥሩ እንሂዳ
**ዓለሙ**:-እኬ/ተያይዘው ይወጣሉ/ሽብሬ ቡናውን ታነሳሳለች/
**እልልታ**:-በይ ለአቶ እሳቱ ቁርሱን ስጪው
**ሽብሬ**:-እሺ ይሄን ቤት ልጠራርግ ስለሆን ጓዳ ይግባና ይብላ
**እሳቱ**:-እሺ/እየገባ ምን ችግር አለው እዚያም ሆነ እዚህ ያው ሆድ ውስጥ ነው የሚገባው/
**እልልታ**:-ነይማ ሽብሬ/ታቀፋትና/ ግን ስለነገርሽኝ ነገር ምን ያህል እርግጠኛ ነሽ እኔኮ በባለቤቴ ላይ ያለኝ እምነት ሁሉ ፀሐይ እንደመታው የበረዶ ከምር እየቀለጠ ከልቤ ሊጠፋ ምንም አልቀረውም እና ያላንቺ የቅርብ አማካሪ ማን አለኝ ፋናዬ እንደሆነች ብዙውን ጊዜ ስለማንገናኝና ብንገናኝም ካላት የሥራ ፀባይ አንፃር ስለጤንነታችን ከመጠያየቅ ስለማናልፍ ሁሉም ገበናዬ ካንቺ የተሠወረ አይደለም እና ምንድን ነው ማረጋገጫው::
**ሽብሬ**:-/የውሸት መልስ ለመፍጠር እየሞከረች/አይ እትዬ ምንድን ነው ማረጋገጫው አልሽ አንቺኮ ምስኪን ነሽ ምነው አሁን እለት እንኳን ጤፍ እንድገዛ ልከሽኝ አልነበር::
**እልልታ**:-አዎን/ዘበኛው ያዳምጣሉ/
**ሽብሬ**:-ታዲያ አስፓልቱን ልሻገር ስል መኪናዎቹን ይኸ ቀዩ መብራት አቁሞአቸው ነበር አለፍ ስል ነው በመኪናቸው ውስጥ ጎን ለጎን ተቀምጠው ሲያወሩ ያየኋቸው::ከዚህ በፊትም ጥርጣሬ ነበረኝ ነገሩ ሁሉ እውነት እንደሆነ ለማረጋገጥ ቻልኩ :: ግን አንቺ እህቴ እንዳትጎጂብኝ ፈልጌ ነው ላለመናገር ዝም ያልኩት::እንዲያውም ዛሬ ጠዋት ቤተ ክርስቲያን ሄዳችሁ ሳለ ስልክ ደውላ ነበር የሉም ብዬ ስላት በኋላ እድውላለሁ ብላኝ ዘጋችው::
**እልልታ**:-( እንደማልቀስ ብላ በሲቃ ድምጽ)አቤቱ ጌታዬና አምላኬ ፍጣሪዬ ሆይ እነሆ በአንተ ፈቃድ ከጌታነህ ጋር አንድ አካል አንድ አምሳል ሆነን በሥጋና ደምህ ቁልፍነት ታስረን ካንተ ሌላ ካንቺ ሌላ ላላይ ተባብለን በጥሩ የትዳር

አቅጣጫ እየተጓዝን ነበር አሁንም ለጊዜያዊ የሰይጣን ጥሪ ጓጉቶና ተታሎ የሚዋዥቀውን የባለቤቴን ልብ አንተ በቸርነትህ አፅናልኝ እነሆ ጌታዬ ሆይ አንተ ከደመና በላይ ከፍ ከፍ ያልክ ነህና የኔን የባሪያህን ጸሎት ከምድር ዳርቻ አድምጥ ስለ እናትህ ስለ ቅድስ ድንግል ማርያም ስለ ፃድቃን ሰማእታት ብለህ የባለቤቴን ፀባይ አስተካክለው የጥንቱን ጌታነህ አድርገው፡፡(እንባዋን ስትጠራርግ አለሙ ይገባል)

**እልልታ**:-ውይ አቶ አለሙ መጣህ

**ዓለሙ**:-እልልታ ምን ሆነሽ ነው አይንሽ የቀላው አልቅሰሻል እንዴ?ምነው በደህና (እየተቀመጠ)

**እልልታ**:-አይ አቶ ዓለሙ ምን በደህና አለቅሳለሁ ብለህ ነው፡፡አንዳንድ የጥርጣሬ ዘሮች በዲያቢሎስ ገበሬነት በኔና በባለቤቴ ልብ ላይ ተዘርተው ፍሬ ማፍራት እየጀመሩ ነው፡፡

**ዓለሙ**:-እንዴት አልገባኝም?

**እልልታ**:-በእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ በሥርዓተ ተክሊል የተሰራ ጋብቻችን ውስጥ የትዳር ደንቃራዎች በዙብን፡፡እየውልህ ጌታነህ በእግዚአብሔር ፊት የገባውን ቃል በመሻር ከመስሪያ ቤቱ አንዲት ልጅ ጋር እንደተዋደደና እኔ በማልኖርበት ሰዓት ስልክ እየደወለች እንደምታናግረው ሰማሁ መስማት ብቻ ሳይሆን በዚህ ሰሞን ያመጣው እንግዳ ፀባይም ሆነ ለኔ ያለው ግምት እየቀነሰ መምጣቱ እንደ ጉልህ ማስረጃ ሆነው ልቤን በጥርጣሬ እና በቅናት ፍላፃ ክፉኛ እየወጉት ነው፡፡

**ዓለሙ**:-በርግጥ ይህን ነገር አድርጎት ከሆነ አንቺ ብቻ ሳትሆኚ እኔም እጅግ አዝንበታለሁ ግን እየሽ አንዳንድ ጊዜ ለወሬኞች ቦታ መስጠት ጥሩ አይደለም ሰምተሽ እንዳልሰማሽ ልታሳልፊው ይገባሻል፡፡ምነው እልልታ ዝም አልሽ ተጫወቺ እንጂ

**እልልታ**:-/እያለቀሰች ከነበረበት ቀና ብላ እየተራመደች/ይህ ነገር ሳስታውስ አንድ ነገር ትዝ አለኝ በልጅነቴ ወሬ ቤተሰባችንን እንዴት እንደበተነብንና እኛን ለችግር እንደዳረገን አስታውሳለሁ አባቴ ሀይለኛና ቅናተኛ ነበር እናቴ ቆንጆና ቤት ክርስቲያን ሳሚ ነበረች የነበረኝ ፤ ታላቅ ወንድም ብቻ ነው ታዲያ የአባቴ ጓደኛ የነበረ አንበርብር የሚባል የሰይጣን ባሪያ አባቴንና እናቴን ለማፋታት የሆነ ያልሆነ ወሬ እየቀባጠረ ለአባቴ ሲነግረው አባቴም በቅናት እናቴን ማታ ማታ እየደበደባት የቤተሰባችን ፍቅር ደብዝዞ የጥላቻ ደመና ረበበበት ታዲያ ይህ ስሙን ልጠራው የማልወደው እኩይ ሰው የሚያወራለት ወሬ ሁሉ አባቴ እውነት እየመሰለው ጥላቻው እየተካረረ መጣ እኛም ሰላም አጣን አቅም ቢኖረን ሰውየውን በወቅቱ ብንገለው ደስታችን ነበር፡፡ሆኖም ግን አባታችንን ተው የሚለው ሰው ባለመኖ አንድ ቀን ሌሊት በደም ፍላት ተነስቶ ሽጉጡን አውጣና እናታችንን ሊገላት ሲል እኛ ደንግጥን ስንጯጯህ አስፈራርቶን መኻታ ቤታችን ውስጥ ቆለፈብን እናታችንም ተንበርክካ ስለ ቅዱስ ሚካኤል አትግደለኝ እኔ ንጹህ ባለቤትህ ነኝ ከማንም ጋር አልወሰለትኩም በማርያም በማርያም ስትለው ተኩሶ ግንባሯን መታት እምየ ሞተች ባላጠፋችው ጥፋት ተቀጠፈች፡፡

**ዓለሙ**:-ታዲ አባትሽ ከዚያ በኋላ ምን ሆኑ?

**እልልታ**:-እጁን ለፖሊስ ሰጥቶ በድሬ ደዋ ከፍተኛ ፴ እስር ቤት ሳለ ቀስ በቀስ እውነቱን ሲረዳ ያደረገው ሁሉ ፀፅቶት ራሱን ሰቅሎ ገደለ እኔም አዲስ አበባ ያለችው አክስቴ መጥታ ወሰደቺኝ ወንድሜ ግን እዛው ጠፍቶ ቀረ፡፡/ተንበርክካ ታለቅሳለች ዓለሙ ተነስቶ ከተንበረከከችበት አንስቶ ደረቱ ላይ ይለጥፋታል፡፡ደረቱ ላይ ሆና ስታቅስ እሳቱ ከጓዳ ሽብሬን አቅፎ ሊወጣ ሲል እነ አቶ ዓለሙን ይመለከታቸዋል፡፡ወዲያው ፎቶ ያነሳቸዋል፡፡ዘበኛው እሳቱ ፎቶ ሲያነሳ ተመልከተው ደንግጠው ይሄዳሉ/

**እሳቱ**:-ምነው ወ/ሮ እልልታ በደህና

**እልልታ**:-አይ ደበህና ነው ስለወንድሜ አስታውሼ ነው ያለቀስኩት

እሳቱ:-እንደዛስ ከሆነ መልካም እኔ ደግሞ በሌላ መስሎኝ በሉ ደህና ዋሉ /ካሜራውን ይስምና ይወጣል/

**እልልታ**:-ውይ መሄድህ ነው በል ቻው፡፡

**ዓለሙ**:-በተቻለ መጠን ወንድምሽ የሚገኝበትን መንገድ ለማመቻቸት እሞክራለሁ ከዚያም ባሻገር ጥሩ መንፈሳዊ ምክሮችን ምሳሌዎችን በመጥቀስ ቅናትን ከልቡ ፈጽሞ እንዲጠፋ በእግዚአብሔር ፊት የገባውን ቃል ኪዳን መዘንጋት እንደሌለበት ከጋደኞቼ ጋር ሆኜ ላሳምነው እሞክራለሁ፡፡/በሉ ልሂድ ብሎ ይነሳል/

**እልልታ**:-አደራ እንግዲህ ካንተ የቀረበ ጓደኛ የለውም እሳቱ እንደሆነ ቀልድ በለው እንጂ እንደ ትልቅነቱ አይመክረውም በማስተዋል በስጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ እውቀት አንተ ስለምትሻል የተቻለህን ያክል ምከረው እግዚአብሔር ካንተ ጋር ይሁን፡፡

**ዓለሙ**:-አሜን

**እልልታ**:-ግን ምነው ቸኮልክ ትንሽ አትጫወትም

**ዓለሙ**:-የለም መሄድ አለብኝ የምደርስበት ቦታ አለኝ በይ ቻው

**እልልታ**:-እሺ/እንደወጣ/ምናለ ሰው ሁሉ ለእኛ እንዳንተ ቢሆን እግዚአብሔር ይከተልህ/ወደ ጓዳ ትገባለች/

/ዘበኛው ሳሎን ውስጥ ገብተው የተሰቀለውን ፎቶ አንስተው አቅፈው ያለቅሳሉ ይስሙታል ወዲያው እልልታ ትገባለች/

**እልልታ**:-ወይ ጋሽ አንዳርጌ ምን እየሰሩ ነው?ደህና ዋሉ

**አንዳርጌ**:-ደህና ደህና ነኝ ልጄ ሽብሬን ፈልጌ ስገባ ፎቶሽ አቧራ ዝበረበትና ጠራርጌ እየሳምኩት ነበር ልጄ ላንቺ ያለኝ አክብሮትና ፍቅር ልዩ ነው ከገዛ አብራኬ የወጣሽ ልጄን ነው የምትመስይኝ::

**እልልታ**:-አይ አባባ ለመሆኑ ልጅ አለዎት

**አንዳርጌ**:-/በመደናገጥ/ አንድ ጎረምሳ ልጅ ነበረኝ ግን ምን ዋጋ አለው በወጣትነቱ በመኪና አደጋ አረፈ::

**እልልታ**:-ውይ በምትኩ ግን እኮ አባባ እኔም ብሆን አባቴን አባቴን ነው የሚመስሉኝ አባቴ ቁርጥ እርስዎን ነው የሚመስለው ነፍሱን ይማረውና::

**አንዳርጌ**:-ታዲያ ልጄ ተጠንቀቂ ጠላትና ወዳጅን ለይ ጠላት ከውስጥ ነው በኋላ ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ እንደሚባለው ያጎረሰው እጅሽ ተነክሶ እንዳትፀፀቺ ጠላትና ወዳጅሽን ከአሁኑ ገምቺ በተፈጥሮሽ ምስኪን የገነት ወፍ ነሽ አንዳንድ ሰዎች በድስትሽ እንዳልበሉ-----(ሽብሬ በር ላይ ቆማ በንዴት )

**ሽብሬ**:-ይስሙኝ መፍለጫው ከነ እንጨቱ ተዘጋጅቷል መጥተው በፍጥነት ይፍለጡልኝ ሰራዬን ልስራበት

**አንዳርጌ**:-/እየወጡ/እኔም እሱን ብዬ ነው የመጣሁት

**እልልታ**:-ሽብሬ በይ ፋናዬ ጋር ደረስ ብዬ እመጣለሁ ጌታነህ ከመጣ እዛ እንደሄድኩ ንገሪው ቤቱንም በወግ በወጉ አስተካክይው/ትወጣለች/

**ሽብሬ**:-እሺ እትዬ(እየተወዛወዘች መጥረጊያዋን ይዛ መድረኩ ፊት ገጽ ላይ ሆና)እከ እንትፍ የሰው ቤት ኑሮ ኤድያ ገረድነት እስከመቼ ተለፍቶ ይዘለቃል ማንም ሃብታም ቢሆን እኮ ሰርቶ በንጹህ ላቡ የሚያገኘው አነስተኛ ህብረተሰብ ነው ሌላው ግን በማጭበርበር በተንኮል ነው የሚያገኘው እኔስ ለዚህ በምን አንሳለሁ በሁለቱ ባልና ሚስቶች መካከል ትንሽ የፀብ ክብሪት በመጫር የሁለቱን መለያየት ተገን በማድረግ በሰው ቤት የወጣትነቴን ወዝ ከማሳለፍ በአቋራጭ የሃብቱ ተካፋይ በመሆን የድህነትን ቀንበር አሽቀንጥሮ መጣል::

**እሳቱ**:-/እሳቱ እየገባ/ትክክል

**ሽብሬ**:-/ድንግጥ ብላ ትዞራለች/ሂድ ያስደንግጥህ እቴ አየህ ና ልቤን ንካው ምን ያህል እንደሚመታ ኮቴ ቢስ ኮቴህ እንኳን አይሰማም ለስሙ ጫማህ ለአስር ሰዎች የሚበቃ የቆዳ ፍጆታ ነው የወሰደው::

**እሳቱ**:-/ጫማውን ከፍ አድርጎ እያየ/ኧረ መተረብሽ ነው እንጂ ካንቺ ኮንጎ አይሽልም::በፀሐይ አድርገሽ ስትወጪ እግርሽ በድግስ ቤት ቀይ ወጥነት የታደመ ቅቅል የበሬ ሥጋ ሲመስል አቤት ሽታው ደግሞ በአፍንጫ ገብቶ በጆሮ ይወጣል::

**ሽብሬ**:-ውይ አልቀረብህም ያንተስ አይሸትም ግማቱ ሰይጣን ያስለፈልፋል መቼስ አልጋ ስር ከተከማቹ ካልሲዎች አንዱን አንስቼ ወርውሬ ግንባርህን ብልህ ደም በደም ነው የምትሆነው::

**እሳቱ**:-/ይስቅና/ ስለደረቀ ማለትሽ ነው አይደል::አዬ በአፍማ መች አቸልሽና እሱን አንተወውና ያንቺም የኔም ሽታዎች በዚህ ቤት በኛ ውስጥ ከነ እልልታ መቃብር በኋላ በእን እልልታ ሞት ይፀዳሉ ለመሆኑ ባንቺ በኩል ያለው እንዴት ነው ከግራ ከቀኝ እያጣደፍሽልኝ ነው::

**ሽብሬ**:-አዎ በእኔ በኩል ያለው እየሰመረ ነው ያንተስ እንዴት ነው ይህንን በግ ደህና አድርገህ እየነዳህልኝ ነው::

**እሳቱ**:-በሚገባ አሁን ንዴት አፍንጫው ላይ ደርሷል አንድ ማስረጃ ብቻ ነው የሚፈልገው ቀይ ሽብሬ ሽቶ አለሽ?

**ሽብሬ**:-አዎ አንዲት ሽቶ አለችኝ

**እሳቱ**:-ጥሩ ሸሚዙን እንደቀየረ ሸሚዙን ቶሎ አንስተሽ ሽቶ ትቀቢና አንደውም አብረው ነው የዋሉት አንቺ ከምታውቂው ሽቶ ሌላ ሽታው የሌላ የሆነ ሽቶ ጋሼ ተቀብተዋል ሸሚዛቸውን ብትፈልጊ አምትጩ ላሽትሽ ትያትና ታሸቺያታለሽ አኬ (በፈገግታ)

**ሽብሬ**:-አኬ(በፈገግታ)

**እሳቱ**:-እንዴ እረስቼው አሁን እኮ ጌታነህ ልኮኝ ነው የመጣሁት

**ሽብሬ**:-ምን ብሎ?

**እሳቱ**:-ካፖርት ልወስድለት ነው የመጣሁት ቶሎ በይ ይዘሽ ነይ የኔ ቆንጆ

**ሽብሬ**:-/ወዲያና ወዲህ ሰውነቷን እያወዛወዘች እያየች)ውይ ቆንጆ ነኝ እንዴ

**እሳቱ**:-ምን ይወጣልሻል ልቅም ያልሽ ቆንጆ ነሽ ይህ ሁሉ ውበት ከዚህ ቤት ንብረት ጋር ዋና ይሆናል ከአንድ አብይ ድል በኋላ/በፈገግታ ወደ ጓዳ ትገባለች/

**እሳቱ**:-አዎ መስሎሻል አንዴ ይሳካልኝ እንጂ አፈር ድሜ ነው የማስግጥሽ ደግሞ ቆንጆ ነኝ ትያለሽ ቋንጣ የመሰልሽ አንቺን አግብቶ ማነው የሚኖረው ዘርፍዬ የት ሄዳብኝ ክልፍልፍ/ካፖርት ይዛ ትወጣለች/አመጣሽ በይ አደራ ዓላማችንን እንዳንረሳ አኬ

**ሽብሬ**:-አኬ/በፈገግታ ወዲያው ሲወጣ ፈገግታዋ ይለወጥና/መስሎሃል ትበላለህ አ ብለህ ጠብቅ ድግሞ እኮ አያፍርም ይህ የጨረጨሰ ሽማግሌ እኔን ሲያገባ ታየኝ ራሱ በሰራው ተንኮል አጠፋዋለሁ እኔም እኩያዬን መፈለግና እንደ እትዬ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እንዳገባ ነው ምኞቴ ይህን ምኞቴን ከግብ እንደማደርሰው ደግሞ አልጠራጠርም/አጎንብሳ ሶፋውን እያስተካከለች/እኔኮ የሚገርመኝ ይሄ በእጁ ያንጠለጠለው አሮጌ ቦርሳ ተወጥሮ እስኪቀደድ ድረስ በሰነድና በብጥስጣሽ ወረቀት ከመሞላቱም በላይ ጥዋትም ማታም ሲተኛ ታቅፎት ሳይሆን አይቀርም የሚተኛው ከእጁ አይለየውም ::አይ እግዚአብሔር እንደ ዶክተር ዓለሙን ተጠብቦ በሰራበት እጁ እንዲያው እንደዚህ አይነቱን ቁልቁላ ሰው ይፍጠር:: ዶክተር ዓለሙ በመልክም በግርማ ሞገስም በእውቀትም በፀባይም የታደለ ነው መቼም እርሱን ያገባች የታደለች ናት ምነው እኔ የሰው ሃብትና ንብረት መመኘቱ ቀርቶብኝ አምላክ ይህን ዶክተር ለኔ ባደረገው አይ ምንኛ እድለኛ ነበርኩ:: /ፋታ/እንዲያው አንዱ መንፈሴ ሃሳቤን አጥብቆ እየተቃወመኝ ነው ብቻ እንጃልኝ

**እንዳርጌ**:-/ላባቸውን በመሀረብ እየጠረጉ ይገቡና ወንበር ላይ ቁጭ ብለው/የተከመሩትን እንጨቶች ጨርሻለሁ

**ሽብሬ**:-ጨረሱ?

**እንዳርጌ**:-ፈልጩ ጨርሼ አስተካክያለሁ ነገር ግን ገና ያልጠረብኩት ልጠርበው የሚገባኝ ግና ያልፈለጥኩት ልፈልጠው የሚገባኝ ነገር አለ::

**ሽብሬ**:-ቆይ ምሳ ላምጣልዎት/ወደ ጓዳ ትገባለች//አንዳርጌ ተነስተው ፀሎት ያደርሳሉ/

**እንዳርጌ**:-አምላኬ ሆይ እርዳኝ አግዘኝ እነሆ ልቧን እንደ ፈርኦን አታደንድነው እሷን መሳሪ አድርጌ ለምሰማራበት ቅዱስ ዓላማ እጠቀምባት ዘንድ ስጠኝ ወጣትነትንና የሷን ልብ ሊያሸንፍ የሚችል እንደበት ስጠኝ ስለኔ ሚስጥራዊነት ካንተ ሌላ የሚያውቅ የለምና የዓላማዬን በር የእርሷን ልብ በመርታት ክፈትልኝ ስለ እናትህ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ብለህ ተለመነኝ እርዳኝ ፈጣሪዬ::

**ሽብሬ**:-(ምግብ ይዛ ትገባለች)

**እንዳርጌ**:-ምን እዚህ ልብላው ብለሽ ነው እጄንም አልታጠብኩም ይልቅ እጥፍ እጥፍ አድርጊያትና ጎጆዬ ወስጄ እበላታለሁ/አጥፋ ትሰጣቸዋለች/

**ሽብሬ**:-ፀሎት እያደረሱ ነው እኔም አሁን ተውኩት እንጂ ፀሎት ሳላደርግ አልበላም ነበር::ግን አባባ ቅድም ልጠርበው የሚገባኝ ያልጠረብኩት ልፈልጠው የሚገባኝ ያልፈለጥኩት ነገር አለ ብለው ያሉት ምንድን ነው?

**እንዳርጌ**:-እየውልሽ ልጄ ልብ ብለሽ አድምጪኝ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሠውን ልጅ ከኃጢአት ነፃ ለማውጣት በመጣ ጊዜ ጴጥሮስ ከወንድሙ ከእንድርያስ ጋር አሳ በማጥመድ ይተዳደሩ ነበር::ከእለታት አንድ ቀን ጴጥሮስና እንድርያስ ቀኑን ሙሉ አሳ በማጥመድ ቢያሳልፉም ጠብ የሚልላቸው ነገር አላገኙም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደእነርሱ መጥቶ በድጋሚ መረቡን ወደ ወንዙ እንዲጥሉት አዘዛቸው እነርሱም አንተ ስላልክ ይሁን እንጂ እኛስ ከጠዋት ጀምረን አንድም አሳ አላጠመድንም ብለው መረቡን ዘረጉት ወዲያው መረቡን ሲስቡት ለማመን እስከሚያስቸግር ድረስ ብዙ አሳ ተያዘላቸው ጴጥሮስም ጌተዬ እኔ በፊትህ መቆም አይገባኝም ሲል አዝኖ ተናገረው ጌታም አይዞህ ጴጥሮስ ና ተከተለኝ ዓሣ ሳይሆን ሰው ታጠምዳለህ አለው::እርሱም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰው አጥማጅ ሆነ እልሻለሁ::እና እኔም ይህን ያልኩት ጴጥሮስ በጌታ ቸርነት ሰው አጥማጅ እንደሆነ ሁሉ እኔም በአምላክ ቸርነት ከእንጨት ጠራቢነት ወደ ሰው ልብ ጠራቢነት ለመለወጥ ፈልጌ ነው::

**ሽብሬ**:-እንዴት?የሠው ልብ ጠራቢና አስተካካይ አልገባኝም ምሳሌዎት ከበደኝ የሰው ልብ እንዴት ይጠረባል በምንስ ነው የሚጠረበው::

**እንዳርጌ**:-እንጨት ተጠርቦ ለአግልግሎት የሚውለው ለአገልግሎት ይውላል ሌላው ለማገዶነት ያገለግላል፣የማያስፈልገውም ይጣላል የሰው ልጂ ልብም አላስፈላጊ የሆኑ ክፋት፣ምቀኝነት፣ቅንዓት፣ተንኮል እና የሰው ሃብት መመኘት/በድንጋጤ ትነሳለች/ የመሳሰሉ አስከፊ ኮተቶችን አዝሏል ስለዚህ ልባችን እነዚህ ይወገዱለት ዘንድ በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ሊጠረብ ይገባዋል::አትደንግጪ ሰው ስለሆንሽ መሳሳትሽ አይቀርም ጥሩው ነገር ግን ስህተቱን ሙሉ ለሙሉ አልፈፀምሽም ስለዚህ ከስህተት ወጥተሽ ሌላ ቅዱስ ፍሬ ልታፈሪ ይገባል::

**ሽብሬ**:-ምን አሉ እርስዎ ማነው የሰው ገንዘብ የሚመኘው እኔ ሽብሬ ዝም ብለው አይቀባጥሩ

**እንዳርጌ**:-ስንተዋወቅ አንተዋወቅ አሉ የሀገሬ ሰዎች ክፉ የማጥፊያ ተንኮልሽን በውስጥሽ እየጠነሰሰሽ ከላይ ሰው ለመምሰል አትጣሪ ከእሳቱ ጋር የተማከራችሁትን ሁሉንም ነገር ድርሼበታለሁ ይልቅ ይቅር ባይ ወደሆነው እግዚአብሔር እራስሽን አስጠጊ::

**ሽብሬ**:-እየውልዎት አወቁትም አላወቁትም ምን አያመጡም ህልሜን ለማደናቀፍ ከፊቴ ከቆሙ አይማረኝ አልምርዎትም :: ይልቅ ጭቅጭቁን እንተወውና ለምን እርስዎ ከእኛ ጋር ተባብብረው የሀብቱ ተጋሪ አይሆኑም

**እንዳርጌ**:-አቤት ድፍረት አቤት አይናውጣነት አንቺ አታፍሪም እንዲህ ፀጉሬ ነጭ ሆኖ የክፉ ስራ ተባባሪ ሁን ስትይኝ::ወይ ጉድ ሞቼ በመገነዣዬ እንዲህ አይነት ግፍ ልሰራ::የእኔ ነገር ተይውና እናንተ ከክፉ ተንኮላችሁ ተቆጠቡ::አለበለዚያ----

**ሽብሬ**:-አለበለዚያ ምን

**እንዳርጌ**፡-ሁሉንም ፍርፕርፕ አድርጌ ለባለቤቱ እናገራለሁ፡፡
**ሽብሬ**፡-እንተያያለና ከዚህ ቤት ወይ ቀድመው ያጠፉናል ወይ እኛ እናጠፋዎታለን፡፡(ልትወጣ ስትል)(ወደ እሷ እየተጠጉ)
**እንዳርጌ**፡-የእግዚአብሔርን የምህረትና የይቅርታ እጅ አትግፊው እባክሽ ወደ ልብሽ አስጠጊው እኔ የአባትነቴን ተናግሬአለሁ ምከረው ምከረው እንቢ ካለ መከራ ይምከረው እንዳይሆን ነገሩ(ይወጣሉ) ( መድረክ ይዘጋል)፡፡

## *መጋረጃ ሲከፈት*

(ሽብሬ ተኝታ ትታያለች)

ድምጽ፡-ልጄ የዋህነት በልብሽ ሞልቶ፣የምትሰሪበት የወጣትነት ጉልበት ሳታጪ፣ሰርተሽ መብላት እየቻልሽ፣ምነው የሰው ትዳር መበጥበጥ አማረሽ፡፡ያንቺ ያልሆነውንስ ገንዘብ ለምን ተመኘሽ፡፡አሁንም ጊዜው አልረፈደም፡፡ወደ ልቦናስ ተመለሽ፡፡የእግዚአብሔርን የጥሪ ድምጽ አዳምጪ ሽማግሌው የመከሩሽን መላልሰሽ አስታውሺ፡፡አይ ካልሽ ዘለዓለማዊ ሞትሽኝ መምረጥሽ ነው፡፡
**ሽብሬ**፡-(ደንግጣ ከእንቅልፏ እየተነሳች)የዋህነት፣ወጣትነት፣ትዳር፣መበጥበጥ፣አለበት መመኘት፣የጥሪ ድምጽ፣ዘለዓለማዊ ሞት ይሄ ሁሉ ምንድን ነው፡፡ መቼም ቅዠት መሆን አለበት እንጂ እውነተኛ ህልም አይመስለኝም፡፡(ፋታ )የለም ከዚህ በፊት እንዲህ ቃዥቼ ስለማላውቅቀ የአምላክ ጥሪ ሊሆን ይችላል፡፡(ተነስታ ወደ አባባ ትሄዳለች) ምንድን ነበር ያሉኝ፡፡
**እንዳርጌ**፡-አይ ልጄ መጣሽ እኔም በዚያ መጥፎ ሀሳብሽ እንደማትጸኚ እርገጠኛ ነበርኩ፡፡ ልጄ ያልኩሽማ የሰው ገንዘብ መርዝ ነው ይልቁንም በጭንቀት ባህር እያሳቀቀ ወስዶ ነው የሚያሳብድሽ«ሊሰራ የማይወድ አይብላ»ይላል ቅዱስ መፅሐፍ ስለዚህ አሁን በላብሽ ሰርተሽ የምታገኚያትን ተመስገን እያልሽ ልትመገቢያት ይገባል እግዚአብሔር አምላክ የፈቀዳት ትንሷ ነገር ልታስደስትሽ ትገባለች፡፡የባልንጀራህን ሃብቱን ንብረቱን አትመኝ ይላል ጌታ እግዚአብሔር በአስርቱ ትእዛዛቱ ነው፡፡
**ሽብሬ**፡-ሠይጣን የማይገባበት ቀዳዳ የለም አባባ፡፡እኔም እየተጠራጠርኩ ነው ይህን ሁሉ ልፈጽም የተነሳሁት፡፡በዚህ በደሌ ምን መካስ አለብኝ? ሌሊት በህልሜ ያናገረኝ መንፈስና የእርስወ መንፈሳዊ ምክር ልቤን ሰብሮታልና ምን እንዳደርግ ይወዳሉ?
**እንዳርጌ**፡-ተባረኪ ልጄ ተባረኪ ተመስገን አምላኬ ተመሰገን አሁንማ ማድረግ የሚኖርብሽ ውዳሴ ማርያም አለሽ?
**ሽብሬ**፡-አዎን!ኧረ እንዲያውም ሰኔ ጎለጎታም አለኝ፡፡
**እንዳርጌ**፡-ከአሁን በኋላ በራሽ ላይ መንፈሳዊ ለውጥ አምጪ፡፡ያቋረጥሽውን ፀሎት ከእንደገና ጀምሪ፣ስራሽን በማይነፋ መልኩ እቤት እትዬን አስፈቅደሽ ቤተክርስቲያን ሳሚ፣ቅዳሴም አስቀድሽ ፡፡ግን ያስተካከልነው ነገር ቢኖርም ገና ልንፈልጠው የሚገባ ነገር አለ፡፡ይህን ብቻዬን መፈፀም ስለማልችል አንቺን የመፍለጫ መሳሪያዬ ላደርግሽ አስቤአለሁ፡፡ አንቺም መሳሪያዬ በመሆን እከአሁን አጥፍቻለሁ ብለሽ ስትፀፀቺበት ለነበረው ጥፋትሽ ካሳ መካሻ ስለሚሆንሽ ልትተባበሪኝ ቃል ግቢልኝ፡፡
**ሽብሬ**፡-/እንደማሰብ ትልና/አሃ!በጥሩ ሁኔታ ተረድቼዎታለሁ፡፡እንዳሉኝ መንፈሳዊ ህይወቴን ፍፁም አለውጣለሁ፡፡ልቤ በምክርዎት ክፉኛ ተረቷል ፡፡ በእውነት አያቴ ቁጭ አድርገው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግሩኝ የነበሩት ነገሮች አሁን ትዝ አሉኝ፡፡
**እንዳርጌ**፡-ወላጆችሽ አሁን በህይወት አሉ?
**ሽብሬ**፡-እናቴ ሞታለች አባቴ ግን አለ፡፡
**እንዳርጌ**፡-የት እዚሁ አዲስ አበባ
**ሽብሬ**፡-አይ ጂማ ነው፡፡እኔ በምልክለት ገንዘብ ነው የሚተዳደረው፡፡ሌላ ምንም የገቢ ምንጭ የለውም፡፡
**እንዳርጌ**፡-አይዞሽ ደግሞ ይሄን ሁሉ ጥረት ለምን እንደማደርግ የምነግርሽ ታላቅ ምስጢር አለ፡፡ጊዜው እስኪደርስ ድረስ ካንቺ እንዳይወጣ ፡፡ወደ ማታ ስራሽን እንደጨረሽ ብቅ በይ አንዲት ቁጨቷን ያልጨረስኳት ነጠላ አለችኝ በዛው እሷን በመቋጨት ታግዢኛለሽ፡፡
**ሽብሬ**፡-ደግ እንግዲህ የሚያጫውቱኝን ምስጢር እጠብቃለሁ፡፡
**እንዳርጌ**፡- እግዚአብሔር ይመስገን ለዚህ ያደረሰን/ይወጣሉ/፡፡
**ሽብሬ**፡-እውነትም የሰው ልብ ጠራቢ/ሙብራት ይጠፋል መድረክ ይዘጋል/መድረክ ሲከፈት
**ጌታነህ**፡-/ፒጃማ ለብሶ ፀጉሩን እያበጠረ/አይ አምላኬ የሠጠኸኝን ጽናት ነጠከኝ ያ ሁሉ መተማመን የት ገባና ነው ዛሬ የጥርጣሬና የቅናት ዝርያዎች በመካከላችን የተፈጠሩት በህልሜ ይሆን?አምናኝ ተማምነን የፈጸምነውን ቅዱስ ቃልኪዳን እኛን ለጭንቀትና ለፀብ ጋብዞን መሄዱ ይሆን፡፡የገዛ ጓደኛዬ ዓለሙ? አይደርገውም ውሸት ነው እርሱ የኔን ባለቤት አያማግጥም ይልቁንም እንደ እህቱ ነው የሚያያት ፡፡ግን ምን ማስረጃ አለኝ ጓደኛህን ውደደው እንጂ አትመነው ነው ተረቱ ምኑ ይታመናል፡፡በእርግጥ እሳቱ ጉልህ ማረጋገጫውን በቃሉ መሰረት ካመጣልኝ ምን እንደማደርግ አውቃለሁ፡፡ግን እኮ እሳቱም እየቀባጠረ ሊሆን ይችላል፡፡ግን ምን ያስዋሸዋል?ምን የሚያገኘው ጥቅም ኖሮት? አንድ ነገር ሳያውቅ አይናገርም፡፡የሆነ ሆኖ አምላኬ እውነቱን አንተው ግለጽልኝ፡፡ቃል ኪዳናችን በአንተው ፍቃድ እውን እንደሆነ ጽናትና ዘላቂነቱንም አንተው አድለን፡፡/ወደ ጓዳ ይገባል ሽብሬ የጠረጴዛና የወንበር ልብስ ይዛ ከውስጥ ትወጣለች/

**ሽብሬ**፡-ግን የጋሼ አንዳርጌ ምስጢር እንዴት ያለ ነው?በጣም ይገርማል በህልሜ ሲታየኝ አደረ እኮ የማይታመን የማይጠረጠር ግን ጊዜው ሲደርስ ይገለጻል/ፈጠን ብላ የወንበሮቹንልብስ ትቀያይራለች/ አቶ አንዳርጌ ይገባሉ/ደህና አደሩ እንዴ ይሄ ነተላ ቁጪቱ ዛሬም አላለቀም እንዴ?

**አንዳርጌ**፡-ደህና አደርሽ ምን ያልቃል ብለሽ ነው፡፡ቀን ቀን አትክልት ስኮተኩት ውሃ ሳጠጣ እውላለሁ የምቋጨው ማታ ማታ ብቻ ነው፡፡ ለዚያውም ድካሙ ስለሚጫጫነኝ ብዙም አላመሽም፡፡ይልቅ ያ እኩይ ከይሲ መምጫው ዛሬ ነው በደንብ ተዘጋጂ፡፡እንዳልኩሽ ምንም ነገር እንዳትሳሳቺ እኔ ከጓዳ እሆናለሁ ዛሬ እዚህ ቤት ያለው ሰይጣን ቀንዱን ተመትቶ በቦታው የሰላም መልአክ የሚተካበት የቀኖች ሁሉ ቀን ነው የሚሆነው፡፡

**ሽብሬ**፡-አዎ ልክ ነዎት እርስዎ ብቻ ይዘጋጁ፡፡በእኔ በኩል እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሳልሳሳት ተልእኮዬን ለመፈጸም ዝግጁ ነኝ፡፡እንዳሉትም በረቂቅ ጋኔናዊ ጥበቡ ሳይታይና ሳይዳሰስ በየሰው ልቦናና በየሰው ቤት እየገባ የኃጢአት አሽከላ ተሸካሚ የሚያደርገው ክፉ ዳቢሎስ ተወግዶ በምትኩ በአምላክ ፈቃድ የሰውን ልቦናና ቤት የሚባርክ ቅዱስ መልአክ መተካት ይኖርበታል፡፡

**አንዳርጌ**፡-እግዚአብሔር ይስጥሽ

**ሽብሬ**፡-በል እሺ እሱ ከመምጣቱ በፊት ያልጨረስከው ስራ ካለ ጨርስ፡፡በኋላ ከምትጣደፍ

**አንዳርጌ**፡-ልክ ነሽ ለነገሩ ብዙም ስራ የለኝ እነዚያን ዶሮዎቹ አውጥቼ መኖአቸውን ልስጥና የቀረኝን አትክልት ውሃ ላጠጣ፡፡ /ይወጣል/

**ጌታነህ**፡-በቃ ብዬሻለሁ በዚህ ምላጭ በሆነ ምላስሽ በመጠቀም እኩይ ድርጊትሽንና ገመናሽን ሊያጥብልሽ የሚፈልገውን የልቤን አንደበት በመልካምና ልብ በሚሰብሩ ቃላት እያሸሞነሞንሽ ልታሰንፊው አትሞክሪ፡፡

**እልልታ**፡-ምንድን ነው ገመናዬ ምንስ ነው እኩይ ድርጊቴ እባክህን ይልቅ ይህን አጉል ጥርጣሬህን ከውስጥህ አውጣና ጣል ፡፡ኑሮአችንን በሰላምና በደስታ እንምራ፡፡

**ጌታነህ**፡-በሰላምና በደስታ/በማሾፍ/ድንቄም እንዲህም ተደርጎ ሰላምና ደስታ የለም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኑሮአችን መካከል እንደ ነቀርሳ በመሆን በመካከላችን ያለውን ጽኑ የቁርባን ቃል ኪዳን አፍርሰሽ እኔንም ለጭንቀት ዳርገሽ ሰው ሰራሽ በሆነ ቃል ኪዳን አለምሽን ልታዪ ነው፡፡ግን አይምሰልሽ ከዚያ በፊት እቀድምሻለሁ፡፡

**እልልታ**፡-ተው እባክህ የምትናገረውን እያሰብክ ተናገር በመካከላችን እኮ ፈራጅ የሆነው ህያው እግዚአብሔር አለ በጊዜአዊ ጥርጣሬ በመነጨ ቅናት አለያም በሰው ከሚነገርህ ማስረጃ ቢስ ወሬ ተመስርተህ በአንተ ላይ ያለኝን እምነትና ግምት እንዲቀንስ አታድርግ ይህንን እግዚአብሔርም አይወደውም፡፡

**ጌታነህ**፡-ማስረጃ ቢስ ወሬ አልሽው አይምሰልሽ ማስረጃው እጄ እንደገባ አንቺንም እርሱንም የማደርገውን አውቃለሁ፡፡ በቅርቡ ከነማስረጃው ፍርድሽን እንደምሰጥሽ አትጠራጠሪ፡፡

**እልልታ**፡-እግዚአብሔር ያውቃል፡፡/ሊወጣ ሲል/ጌትዬ ምነው ጨዋታዬ እንኳን አልናፈቀህም፡፡እባክህ ሁሉንም ተወው እኔ ንጽህት ባለቤትህ ነኝ

**ጌታነህ**፡-/በትካዜ እንደመቆየት ይልና/ግድ የለም/ሊወጣ ሲል/

**እልልታ**፡-ኧረ ለአፍህ እንኳን ትንሽ ቁርስ አድርግ/ትቷት ይወጣል ከዓለሙ ጋር መንገድ ላየ ይገጣጠማሉ፡፡

**ጌታነህ**፡-ዓለሙ እንደምን አደርክ

**ዓለሙ**፡-ደህና እግዚአብሔር ይመስገን ምነው ጌታነህ ደህና አይደለህም እንዴ?

**ጌታነህ**፡-አይ ደህና ነኝ

**ዓለሙ**፡-ብትቆይብኝ እኮ ነው ምን ሆኖ ነው ብዬ አመጣጤ?

**ጌታነህ**፡-ምነው ታዲያ ስልክ አትደውልም ነበርምን አደከመህ እዚህ ድረስ/በአሽሙር/

**ዓለሙ**፡-ለስራ እዚህ አካባቢ ነበርኩና እግረ መንገዴን ሰላም ብያችሁ አብረን እንውጣ ብዬ ነው፡፡

**ጌታነህ**፡-ነው!በል እሺ እንሂድ ሠለስት እንኳን ጠዋት ነበር የሚደረሰው ቢሆንም ከሚቀየሙን እንድረስ፡፡

**እልልታ**፡-ውይ ለካ የካሳሁን እናት ሰልስት ዛሬ ነው፡፡

**ዓለሙ**፡-አዎ እንሂድ በል እሺ በይ ወ/ሮ እልልታ ደህና ዋይ

**እልልታ**፡-አሜን ደህና ዋል፡፡አምላክ ሆይ ምነው ጨከንክብኝ አልሰማሽ አልከኝ እውነተኛ ፍርድን ተጠምቻለሁ፡፡ሰዎች ፍረዱን ባላጠፋሁት ባልበደልኩት በደል የእናቴ እጣ ለእኔም ሊደርሰኝ?እኔ ግን የሰራሁት አንዳች ወንጀል እንደሌለ ስለማምን የፈለገውን ማስረጃ ቢያመጣ ከሀቀኝነቴ አያዛንፈኝም-------------------

**ሽብሬ**፡-/ቁማ ታዳምጥ ነበርና እንባዋን በእጇ ጠራርጋ/አይዞሽ እትዬ የዚህ ቤት ሰላምና ፍቅር ልክ እንደ ጥንቱ እንደሚመለስ አትጠርጠሪ እግዚአብሔር በእውነት እንባሽን ይቆጥርልሻል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እዚህ ቤት ጨቅላ ሰይጣን ቀንድ አውጥቶ በስጋ ወደሙ ቋሚ ምሶሶነት ቆመውን የቤቱን ሰላምና ፍቅር ክፉኛ እየተተናኮለ ነው፡፡በቅርቡ ግን ቀንዱን ተመትቶ እንደሚጠፋ እመኚ፡፡

**እልልታ**፡-እንደ አፍሽ ያድርግልኝ ሽብሬ መቼስ የአምላክ ፍቃዱ ከሆነ እሱ ያሻውን ያድርግ ሁሉንም በፀጋ መቀበል ነው፡፡ አንቺን መጽናኛ አድርጎ የሰጠኝ አምላኬ አሁንም ፀጋውን አይንፈገኝ፡፡

**ሽብሬ**:-ይህን ሁሉ ዓመት ስኖር እንኳን ፀብና ተራ አለመግባባት እንኳን ሰምቼ አላውቅም::በመካከላችሁ ግን እግዚአብሔር ሊፈጽመው ያሰበው አንድ ተዓምር ቢኖር ነው::ሌሎች ይማሩበት ዘንድ ሊፈትናችሁ አስቦ ይሆናል::
**እልልታ**:-እስቲ ይሁን በይ እኔም ልሂድ ወደ ኋላ ምሳ ሰርተሽ ጠብቂን እንዳትረሺ/ትወጣለች/ሽብሬ ጋዜጣ አንስታ ግጥም ታነባለች/

**ሰ/ት/ቤት**

ሰ/ት/ቤት የህይወት መሰረት
ታስተምረናለች የጣፈጠ ትምህርት
ሰዎች ቸል አንበል ይህንን በረከት
ያሰጠናል ከአምላክ ዘንድ ምህረት
የሃይማኖት ትምህርት ከመዝሙራት ጋራ
ዝማሜ ወረቡን ሁሉን በየተራ
ታስተምረናለች ጾማገን ከቀኖና
በአንድ አጣምራ
ወጣት ለማስተማር በግብጽ ተመስርታ
በአገራችንም እጅጉን ተስፋፍታ
ታስተምረናለች መጽሐፍ ዘርግታ
ወጣት ሆይ አደራ እባክህ አትስነፍ
በቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም ተሳተፍ
በእምነት ላይ እንዲሰጥህ ብርታት
ሰይጣንን ለመርታት እንድታገኝ ድፍረት
አደራ አትጥፋ ሰ/ት/ቤት

እንዴት የምትገርም ግጥም ነች እውነቱን ነው እኔ እንኳን ሰ/ት/ቤት መሳተፍ ከጀመርኩ ወራትን አሳፈአለሁ በሃይማኖት እውቀቴም ሆነ በእምነቴ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣቴን አምናለሁ::ሕይወቴ ሁሉ በመልካም መንፈስ የተሞላ ነው::ባን ወገን ፍርሃት ፍርሃት ይለኛል ግን የሚያስፈራኝ ማነው እግዚአብሔር መመኪያዬ ነው አይደለም የሚለው ቃሉ የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማነው አምላኬ መመኪያዬ ነው/ትዘምራለች/ በእርግጥ ወጣቱ ሁሉ እኮ በሰ/ት/ቤት ቢሳተፍ ኖሮ ጥርጣሬ ፣ክፉ ማሰብ ይቀር ነበር::ብቻ የአምላክ ፍቃድ ይሁን/ ወደ ጓዳ ትገባለች ክላሲካል ይለቀቃል//እሳቱም አንዳርጌም እኩል ሲገቡ ይገራመማሉ/
**እሳቱ**:-አንተ ሽማግሌ አሁንም አልሞትክም እዚህ ሳሎን ምን ታደርጋለህ እዚያው እግሮህ ሄደህ አዛባህን አትዝቅም ምን ይመስላል
**አንዳርጌ**:-እስቲ ይሁን ችግር አስረጅቶኝ እንጂ በዕድሜማ ካንተ የምበልጥ አይደለሁም::ነገሩ እንዴ እሰው ጉያ ከተወሸቅህ እንደ መዥገር ተጣብቀህ ደሙን ካልመጠጥክ አትተው::የሰው ቤት ጮማና ጠጅ ነው ወጣት ያስመሰለህ::
**እሳቱ**:-ዝም በል እንዲያውም ሳይህ ገና ነው ደሜ  የሚፈላው::
**አንዳርጌ**:-የማጋልጥህ እየመሰለህ
**እሳቱ**:-ምኑን
**አንዳርጌ**:-ተወው ብቻ እኔም ሳይህ ከዚያች ከምናውቃት ቀን በኋላ እንደምትረበሽ አስተውያለሁ::
**እሳቱ**:ካንተ ጋር ደግሞ ምን አገናኝቶን ነው ቢጋራ የምናውቃት ቀን ያለችው ዝምብ ብለህ ጠጅህን ላፍ ጠጃም
**አንዳርጌ**:-ከካቲካላ ሳይሻል አይቀርም ቢያንስ አንጀት አይልጥም አንተ አለህ እንጂ ሌባ
**እሳቱ**:-ማናባህ ነው ሌባ አንተ
**አንዳርጌ**:-ኧረ እባክህ አንተ ሰው ክብርህን ጠብቅ ከልቤ የጌቶችን ትእዛዝ የረገጥኩ ስለመሰለኝ ነው እንጂ አንተን በዚች ከዘራ ቆማምጦ ማስቀመጥ ከባድ ሆኖ አይደለም::
**እሳቱ**:-እኔ እሳቱ አይደለሁም የእንጀራ ገመድህን ለበጠስኩ እንደሆን ከዚህ ቤት ተባረህ በየመንገዱ ትለምናታለህ ደሞ ሌባ ትለኛለህ ምን ስሰርቅ አይተኸኛል
**አንዳርጌ**:-ምነው ተራሳሳን እሳቱ አሁንለታ እዚህ ቤት ድግስ ንደነበር የማንኪያና የሹካ መዓት በኪስህ ከተህ ስትወጣ ይገፍህ ለጌቶች ላስይዝህ ስል በሰማይ በምድር ተማፅነህ እግሬ ስር ወድቀህ እንዳልናገርብህ አልለመንከኝም::
**እሳቱ**:-ማ እኔ/ሊማታ እጁን ሲቃጣ/
**አንዳርጌ**:-በላ ሞክረኛ/ዱላቸውን ከፍ ያደርጋሉ/
**ሽብሬ**:-ምንድን ነው ነገሩ እንዴት የትልቅ ሰው ቤት ትደፍራላችሁ ነውር አይደለም እንዴ
**እሳቱ**:-እንዴ ሽብሬ ከበር አላስገባ ማለት ብቻ ነው እኮ የቀረው::ቆይ ለጌታነህ ሁሉንም ነገር ነግሬ ያላሽቀነጠርኩት እንደሆን እኔ አይደለሁም

**ሽብሬ**:-በቃ ተወው ለዛሬ እኔ ላስታርቃችሁ /ወደ እሳቱ ጠጋ ብላ/አንተ ደግሞ ይሄን ሽማግሌ አስወጥተህ ምን ይሰራልሃል እኔ እቆጣዋለሁ።።ስሙኝ እርስዎ ብለው ብለው ሳሎን ድረስ መጥተው ከእንግዳ ጋር መጣላት ጀመሩ።።ቀት ብለው ስራዎን አይሰሩም።።

**እንዳርጌ**:-አይ እንደሱ አይደለም እሱ እራሱ ነው ጥፋተኛ እኔ እቤቴ ነው ያለሁት መጥቶ የተጣላኝ እርሱ ነው።።

**ሽብሬ**:-በሉ ወደ ስራዎ ይቀጥሉ እዚህ መከራከር አስፈላጊ አይደለም/ሽማግሌው ይወጣሉ/አንተስ ምን ከዘበኛ ጋር አፍ አካፈተህ ንቀህ አትተዋቸውም

**እሳቱ**:-መቼ የዋዛ ሆኖ ንቄ እተወዋለሁ እናዳውም ሳየው የማላውቀው ስሜት ሰውነቴን ይወረኛል እኔ እንጃ ብቻ ይከብደኛል።።እሱም የሚያየን የልብን ጓዳ ጎድጓዳ የሚበረብር በሚመስል መልኩ ስለሆነ ገና ለገና ሚስጥሬን ሁሉ አውቆብኝ አላማ ላይ እንደተሰቀለ ባንዲራ ግልጽ የሚያደርገው ስለሚመስለኝ ከእሱ ጋር በተገናኘን ቁጥር ሳልሸበር በሰላም አድሬ አላውቅም።።

**ሽብሬ**:-አንተ ደግሞ የዚህን ያክል አታካብደው።።እንዲያውም መስሎህ ነው እንጂ የመጨረሻ የዋህ ነው።።የሆነው ሆኖ የሚያስቸግር አይነት ከሆነ ከዚህ ማስነቀል አያቅተንም።።ብዙም በዚህ ላይ በመጨነቅ አዳዲስ ሽረባ ዘዴዎችን በመዘየድ ተወዳዳሪ የሌለውን አእምሮህን ሰላምአትንሳው ። እድሜ ለአንተ በስንት አመቱ እኔም የህይወት ጣእም ጭላንጭል በተስፋ ጭለማ ተዳፍኖ የኖረውን ሁለንተናዬን የብርሃን ድባብ እንዲያብበት ልታደርገው ነው።።

**እሳቱ**:-ልክ ነሽ ይህን ሽማግሌ ከዚህ ማስወገዱ ሴራችንን በተገቢው መንገድ እንድንፈጽም ከፍተኛ ድርሻ ከማበርከቱም በላይ ለአላማችን መሳካትና እውን መሆን ራሱን የቻለ ማረጋገጫ ነው የሚሆነው

**ሽብሬ**:-በል እስቲ ቆይ ሻይ ላምጣልህ/ብላ ወደ ጓዳ ትገባለች እሳቱ ሳያያት በምልት ከሽማግሌው ጋር በምልክት ትነጋገራለች/እንካ ጠጣ /ይቀበላታል/በጣም ግሩም ሰው ነህ አመጣጥህ የተቀጣጠርንበትን ቅዱስ ቀጠሮ ሳታዛንፍ ስለሆነ በቀጠሮ አከባሪነትህ ወደር የለህም።።

**እሳቱ**:-ምን ይደረግ ብለሽ ነው እንጀራ አይደል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይገርምሻል እያንዳንዷ ሰዓት ለኔ ብርቅ ናት።።

**ሽብሬ**:-አሁን እንቀጥል ወይስ አረፍ ትል

**እሳቱ**:-አይ አንቺ እየነገርኩሽ ምን እረፍት ይስፈልጋል ይልቁን ጊዜ ስለሌለኝ ወደ ዋናው ጉዳያችን እንግባ እኔ በኔ በኩል መደረግ የሚገባቸውን ነገሮች አጠናቅቄ እየጨረስኩ ነው።።የቀረኝ ነገር ቢኖር ጌታነህን ጎትጉቶና ጨቅጭቆ ሕጋዊ ውክልና ለእኔ እንዲሰጠኝ ማድረግና ከፍርድ ቤት ማስጨረስ ነው።።ይህም ብዙ ጊዜ አይወስድብኝም።።ይገርምሻል ፎቶ ግራፉ ከጠበቅኩት በላይቆንጆ ሆኖ ለጌታነህ ሰጥቼው በንዴት እሳት እንደነካው ፀጉር እየተንጨረጨረ ነው።።መቼም ከሄደበት ሲመለስ ዛሬውኑ ከቤት መንግሎ እንደሚያስወጣት እርግጠኛ ነኝ ይህም ካልሆነ ገድሏት እሱም የእሷን ጽዋ እንደሚቀበል አልጠራጠርም።።የሁለቱም እሬሳ ከዚህ ቤት እንደወጣ ከጥቂት የሀዘን ጊዜ በኋላ በተሰጠኝ ሕጋዊ ውክልና መሰረት ይህን ቤት ከአንቺ ጋር ወርሰን ለዘለዓለም መኖር።።

**ሽብሬ**:-/ወደ ጓዳ ምልክት በመስጠት/ልክ ነህ እስከ ዛሬ በጉጉት ስናልመውና ስንጠብቀው የነበረው ህልማችን በሁለቱ ሰዎች ሞት እውን ሊሆን የቀረው የሰዓታት ግፋ ቢል የቀናት ጊዜ ብቻ ነው።።እንዲያውም ዛሬ ጠዋት እርስ በእርሳቸው ሊባሉ ምንም አልቀራቸውም።።መላ ቅጣቸው የጠፋ ሆኗል።።

**እሳቱ**:-ዛሬ ሲጣሉ ነበር ያልሽው እውነትሽን ነው ይህ እጅግ በጣም ጥሩ የሆነ ዜና ነው።።እንደምታውቂው ጌታነህ ለመለስለስ ትንሽ ጊዜ እንዲሁም በንዴት ነብር ለመሆን ትንሽ ጊዜ ነው የሚወስድበት።።በዚህም ምክንያት በትንሽ ንዴት ከባድ እርምጃ ከመውሰድ ወደ ኋላ አይልም እስኪ ይታይሽ ከሁለቱ የዘለዓለም እንቅልፍ በኋላ የሚገኘው ድንቅ ሀብትና ንብረት መኪናው ይህን የመሰለ ድንቅ ቪላ ከነቤት ቁሳቁሱ ፤እንኳን ተቆጥሮ ታፍሶ የማያልቀው በባንክ የሚገኘው ዶላር ሁሉ የኔና ያንቺ ሆኖ ልጆች ወልደን ከብደን ለልጅ ልጆቻችን ሲተርፍ ይታይሽ ሽብሬ።። ስለዚህ አንቺም አሁን እሷ ስትመጣ የበለጠ ግላ ተጋግላ እንድትጠብቀው የነገር መርዝሽን በጥሩ ቃላት ቀምመሽ አጉርሻት እየተናነቃትም ቢሆን ትዋጠው እኔም በኋላ ስመጣ በይፋ እንደምትበድለው እመሰክራለሁ።።

**ሽብሬ**:-/ወደ ጓዳ ምልክት በመስጠት/እሺ የኔ ጌታ የተናገርከኝ ነገር ሁሉ ስሜቴን በጉጉት አነሳስቶ የጊዜውን እውን መሆንና መድረስ በናፍቆት እንድጠብቀውና ለዚህም በእኔ በኩል ማድረግ የሚገባኝን አስተዋጽኦ እንድፈጽም አበረታትቶኛል።። የዚህን የሽማግሌ ነገር ለእኔ ተወው አትፍራ አርፎ ስራውን ይስራ።።እኔ አስጠነቅቀዋለሁ።።ለማንኛውም የድሆች አምላክ አንድዬ ይርዳን።።

**እሳቱ**:-አልተሳሳትሽም የእሱ የአንድዬ እርዳታ ይታከልበት እንጂ እኛማ ብቻችንን እንዴት እንወጣዋለን።።ግን ይህን ዘበኛ ዛሬውኑ ከዚህ ቤት ብታስመነቅሪው ነፃ ሆኜ ስራዬን በተገቢው መንገድ እወጣው ነበር።።እነሱ ሲጣሉ ግን ወደዚህ ሳሎን ብቅ እንዳይል አድርጊው።።

**ሽብሬ**:-መልካም እንዳልከኝ አደርጋለሁ።።ዛሬ እዚች ቤት ድርሽ አይላትም ።።እዚያው እንጨት ሲፈልጥ እንዲውል አደርጋለሁ።።

**እሳቱ**:-ጥሩ በይ አሁን ፍርድ ቤት ድርሼ ልመለስ

**ሽብሬ**:-በል ወደ ኋላ ፈጥነህ ተመለስ ይቅናህ።።

እሳቱ:-እሺ እመለሳለሁ

ሽብሬ:-/በፈገግታ ወደ መሬት ሰግዳ/ተመስገን አላማዬን ልታሳካልኝ ነው ምን ይሳንሃል፡፡ምጡ እየተካረረ ነው፡፡ሀዘኑም ደስታውም ሊወለድ ምንም አልቀረውም፡፡የቅዱሱ ድል ውጤት ፍሬአማ መሆኑ ምንም አያጠራጥርም/ወደ ጓዳ ትገባለች ክላሲካ ይከፈታል ወዲያው እልልታና ጌታነህ ተከታትለው ይገባሉ ጌታነህ ከኪሱ ፎቶ ግራፉን እያወጣ ይመለከታል/

እልልታ:-እባክህ የማውቀው ነገር የለም አትጨቅጭቀኝ በከንቱና በማይረባ ጥርጣሬ ህሊናዬን ሰላም አትንሳው

ጌታነህ:-ዝም በይ! ዛሬ ያንቺና የውሽማሽ ሌብነት የተረጋገጠበት ቀን ነው፡፡ በመካከላችን አንድነት እንዲኖር መለያየት መወሳለት እንዳይኖር በክርስቶስ ክቡር ሥጋና በም ያተምነውን ማህተም እፍርሰሽ በውስልትና ጎዳና ብቻሽን ጉዞ ጀመርሽ፡፡ግን አትጨርሺውም እቀጭሻለሁ፡፡

እልልታ:-ለመንኩህ ላስረዳህ ሞከርኩ--------

ጌታነህ:-/ያቋርጣትና/ለመንኩህ ላስረዳህ ሞከርኩ /በማንቋሻሽ/ሰማሽ እነዚህ ውብ የቃላት ድርደራዎችሽ የድሮውን ጌታነህን ያታለሉት አይበቃቸውም የአሁኑ ግን ሞኝ አይምሰልሽ እውነቱን ልንገርሽ አለሙ ውሽማሽ ነው፡፡

እልልታ:-ነው

ጌታነህ:-አዎን

እልልታ:-ደግ አደረገ/ጌታነህ በጥፊ ይላታል ሊደግማት እጁን ሲዘረጋ የአትክልት ቢላዋ አንስታ/ከአሁን በኋላ እንዳትጠጋኝ ወየውልህ፡፡

ጌታነህ:-/ይስቃል/

እልልታ:- አዎ እንዳትነካኝ/እያለቀሰች/ምነው ጌታነህ እስከዛሬ እንኳን ልትመታኝ ክፉ ቃልም ከአንደበትህ ወጥቶ አስቀይመኸኝ አታውቅም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ፀባይህ ሁሉ ተቀያይሮ እኔን  የጎሪጥ ትመለከተኛለህ፡፡ነገሩ እንዲህ ከምታሰቃየኝ እንካ ግደለኝ/ቢላዋውን ልትሰጠው እጇን ትዘረጋለች/

ጌታነህ:-ለእሱ አትቸኩይ ግድ የለም እያንዳንዳችን እንደርስበታለን፡፡

እልልታ:-የጥንቱ የፍቅረኛነት ጊዜአችን እንደምን ተረሳህ፣በቅዱስ ስገውና በክቡር ደሙ የተመሰረተው ጋብቻ እንዴት ተረሳህ ያ በሳቅ በፈገግታ የሚሞላው ቤታችን ሰይጣነዊ የሸረሪት ድር እንደምን አደራበት በሰው ወሬ መመራት የፍቅር ፀር መሆኑን አበክረህ ትነግረኝ አልነበረም ታዲያ ያ ሁሉ መከባበር ቀርቶ ያ ሁሉ ምክክር ቀርቶ በሰው ወሬ እንዲህ እንታመስ፡፡

ጌታነህ:-እኔ ጌታነህ በወሬ የምመራ ሰው አይደለሁም በማስረጃ አምናለሁ ያለማስረጃም አልናገርም፡፡

እልልታ:-ምንድን ነው ማስረጃህ ይልቅ እኔስ ባለቤትህ ነኝ ጓደኛህን ግን በአጓጉል ጥርጣሬ አስቀይመህ እንዳታስቀረው፡፡

ጌታነህ:-/ይስቃል/አዎ እንዲቀርማ መች ትፈልጊያለሽ ይህን እኮ ማንም ሰው ያስተውላል፡፡

እልልታ:-ኧረ ቃሉ ይክበድህ እኔስ ክብሩ ይሰፋ ለመድኃኔዓለም እራሴን ያስከበርኩ ከአንተም ጋደኞች ሆነ ከስራ ባልደረቦቼ ጋር ከወንድማዊ  ግንኙነት ሌላ አንተ እንደምትለው ግንኙነት የሌለኝ ተዋህዶ በሰ/ት/ቤቱ አማካኝነት ጡቷን አጥብታ ያሳደገችኝ ሴት ወይዘሮ ነኝ፡፡

ጌታነህ:-ተዋህዶማ እኛንም እንደ እናት ተንከባክባ አሳድጋናለች፡፡ ግን እሷ ያስተማረችሽን ሥርዓት ዘንግተሽ ያፈነገጥሽ አንቺ ነሽ፡፡

ዓለሙ:-/ዓለሙ ይገባል/ምነው ሰላም አይደላችሁም እንዴ

ጌታነህ:-እንኳን ደህና መጣህ ዶክተር

ዓለሙ:-/በፈገግታ/ምነው ዛሬ በሞያ ስሜ ጠራኸኝ

ጌታነህ:-አንዳንዴ ሰዎችን በሞያ ስማቸው ስጠራቸው ደስ ይላቸዋል በተለይ በውሽማቸው ፊት

ዓለሙ:-/መነጽሩን አውልቆ/ምን አልክ ጌታነህ

ጌታነህ:-ያልኩትን ብያለሁ

ዓለሙ:-እንዴት ነው ዛሬ ልክ አትመስለኝም እልልታ ምን ሆኗል

እልልታ:-በሰው ወሬ አልያም በገዛ እራሱ ከንቱ ጥርጣሬ እኔን ከአንተ ጋር ወስልተሻል ብሎ ነው እንዲህ የሚሆነው፡፡

ዓለሙ:-ከእኔ ጋር ማለት አንቺና እኔ

ጌታነህ:-አዎ ካንተ ጋር አንተና እሷ እስከዛሬ በእኔ ላይ የቀልድ ኳሳችሁን ስትጫወቱብኝ ነበር ግን አሁን ይበቃል ፊሽካ ተነፍቶ አብቅቷል፡፡  አትልፋ ሁሉንም ነገር ደርሼበታለሁ፡፡አምንህ ነበር ካንተ ባይበልጥም አምናት ነበርየሰው ወሬ የሚለውን ሁሉ የምቀበል አይደለሁም ከእናንተ የእለት ተእለት ሁኔታ ከማስተውለው እና ከምታዘበው ባሻገር በቂ የሆነ አሳማኝ ማስረጃ ይገኛለሁ፡፡

ዓለሙ:-ተው ጌታነህ አትሳሳት አምላክ ይህንን አይወድም፡፡እኔኮ ሚዜአችሁ፣ሸማግሌአችሁ ነኝ፡፡ለናንተ ሰላም ጤና እና ፍቅር ከመመኘት ሌላ ፍቅራችሁን የሚያደፈርስ የሚያለያይ መንገድ የማመጣ ከሆነ እናንተስ ተውት አንድ ያደረጋችሁ የጌታ ሥጋና ደሙ ምን ይለኛል ምንስይፈርድብኛል ተው አታስቀይመኝ ጌታነህ

**ጌታነህ**፡-ተወው ነገሩን ለማስተባበል የተጠቀምከውን የአነጋገር ዘይቤ አደንቀዋለሁ፡፡ነግር ግን ፊት ለፊት እጅ ከፈንጅ እስከምይዛችሁ አልጠብቅም ወንድ ነኝና የወንድነት ስሜቴም አይፈቅድልኝም ከዚህ በላይ ምን ስትሆኑ ልያችሁ

**ዓለሙ**፡-ጥሩ እኔም በእንደዚህ አይነት ተራ ምክንያት ልታጣኝ የምትፈልግ ከሆነ እንኳን ከባለቤትህ ከአንተም ጋር ግንኙነቴ ያበቃል/ሊወጣ ሲል/

**ጌታነህ**፡-/ሽጉጡን መዝዞ/አትወጣም ዶክተር ዛሬ የእኔ የበቀል ቀን ነው /ዶ/ር ወደ ኋላ ይመለሳል//እልልታ ልትወጣ ስትል/ወዴት እልልታ ወደዚህ ነይ ዛሬ የሦስታችንም ደም እዚህ ይፈሳል፡፡

**እሳቱ**፡-(ይገባል)እንዴ ጌታነህ ዛሬማ አልጋ ላይ ሲዳሩ አግኝተሃቸው መሆን አለበት፡፡ነገሩ ለወትሮውስ ቢሆን አልጋህን ደፍሮት ነበር፡፡

**እልልታ**፡-እሳቱ አንተም ይህን አልክ

**እሳቱ**፡-አዎ እልልታ ጌታነህ ጋደኛዬን ስታስደፍሪው መቼስ እያየሁ እንዴት ዝም እላለሁ

**ዓለሙ**፡-ምን አፍህን ትከፍታለህ ለካ ይኽ ሁሉ ያንተ የተንኮል ሸረባ ውጤት ነው፡፡ለመሆኑ እኔና እልልታን የት ነው ያየኸን፡

**እሳቱ**፡-ምን እኔን ትጠይቀኛለህ እሱን ጠይቀው እንጂ

**እልልታ**፡-ተው ጌታነህ ያለምንም ማስረጃ በወሬ አትመራ

**ጌታነህ**፡-ተንበርከክ ተንበርከኪ ዛሬ ደማችሁን አፍስሼ የኔም ደም ይፈሳል እንካችሁ /ፎቶውን ወደ ተንበረከኩበት ይወረውረዋል ሁለቱም በአንድነት ብድግ አድርገው ይመለከቱታል//እሳቱ በደስታ ተመስገን ይላል እጁን ወደ ላይ አንስቶ ሽብሬና ሽማግሌው ይገባሉ/

**እሳቱ**፡-ይሄ ደግሞ ምን ሊሰራ መጣ

**ጌታነህ**፡-አያችሁት በቤቴ ተቃቅፋችሁ በህይወቴ ስትቀልዱ ዛሬ ደግሞ እኖ በተራዬ በእናንተ ህይወት ላይ ቀልጄ በራሴም እፈርዳለሁ፡፡

**እልልታ**፡-ኧረ እባክህ ጌታነህ ተው

**ዓለሙ**፡-ኧረ  ተው ጌታነህ

**አንዳርጌ**፡-ጌታነህ ተው አትቸኩል ኋላ እንዳትፀፀት «ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ነውና ነገሩ እራስህን አታታልል ጠላትና ወዳጅህን ለይ ወንጀል አትፈጽም ቆይ ረጋ በል/ጌታነህ የደገነውን ሽጉጥ ወደ ታች ሲል እሳቱ/

**እሳቱ**፡-አንተ ሽማግሌ ሞት አማረህ  አርፈህ ሂድና በርህን ጠብቅ

**አንዳርጌ**፡-ጌታነህ አንድ የመጨረሻ እድል ለእኔ ስጠኝ ስለ ሁሉም ነገር ልንገርህ እረጋ በልና አድምጠኝ

**ጌታነህ**፡-እሺ የሚያውቁትን ሁሉ ይንገሩኝ ለመጨረሻ ጊዜ ልስማዎት /እሳቱ በንዴት ወደ ሺብሬ ዞሮ በምልክት ያናግራታል አንዳርጌ ድፍረት በተሞላበት አነጋገር/

**አንዳርጌ**፡-ጠላትህንና ወዳጅህን ለይ ጌታነህ ኋላ እጄን በአጂ እንዳትል የዚህ ቤት ጊዜአዊና ኃይለኛ የፀብ ክብሪት ገና ሊጫር ከፓኮው ሲወጣ አውቀዋለሁ፡፡ጌታነህ ብታምነኝም ባታምነኝም ጠላትህ ያቀረብከው ወዳጅ ያደረከው እሳቱ ነው፡፡

**እሳቱ**፡-ዝም በል ምን ይላል ይሄ

**አንዳርጌ**፡-አንተ አይደለህ የሰው ቤት የምትበትን አስተውል ጌታነህ ባለቤት ወ/ሮ እልልታ ንጽህት ባለቤትህ ጓደኛህ ዶክተር ዓለሙ ንጹህ ጓደኛህ ነው፡፡ሁለቱም ከተባለው ነገር ነጻ ናቸው የተለየ ግንኙነት የላቸውም፡፡

**እሳቱ**፡-አላቸው! ምን ይላል ይሄ ሽማግሌ እራሱ ጌታነህ ፎቶ ግራፉን አይቶ ያረጋገጠውን አንተ ትቀባጥራለህ፡፡

**አንዳርጌ**፡-ጌታነህ አንተ ማስረጃ ብለህ የያዝከው የአቶ እሳቱ የሴራ ውጤት ነው፡፡

**እሳቱ**፡-በቃ በቃ ዝም በል!ጌታነህ እኔንስ እሺ ይህ ሽማግሌ እንደተናገረው ላታምነኝ ትችላለህ ስለሁለቱ ግንኙነት ግን የቤት ሰራተኛህ ሽብሬ ትመስክር /ሁሉም በጉጉት አይኗን ያዩአታል/

**ሽብሬ**፡-አዎን ትክክል ነው/እሳቱ ደስ ይለዋል/የዚህ ሁሉ ፀብና ክርክር ሴራ እና ጥንስስ የእሳቱ ነው፡፡/እሳቱ በድንጋጤ ይርበተበታል/ እትዬ ኪጋሼ ዓለሙ ጋር አንዳች የተለየ ግንኙነት የላትም ቅድም እንዳልኩት ይህ የእሳቱ ስራ ነው፡፡

**እሳቱ**፡-ዝም በሉ አለምንም ማስረጃ አትለፍልፉ

**አንዳርጌ**፡-ለወንጀለኛነትህና ለማስረጃው አትቸኩል ሽብሬ ማስረጃችንን ለጌታነህ ስጪው/ሽብሬ ከሸርጧ ውስጥ አውጥታ ካሴት ትሰጠዋለች/

**ጌታነህ**፡-ምንድን ነው ማስረጃው ምንድን ነው የማየው

**አንዳርጌ**፡-ጌታነህ ስሜታዊነት ጋርዶህ እንጂ ሀቁን ታውቀዋለህ፡፡ለማንኛውም በእርጋታ አድምጠው፡/ካሴቱን ቴፕ ውስጥ ይከቱታል እሳቱ  የተናገረው ሁሉም ይሰማል/በዚህ የተንኮል ሰንሰለት ውስጥ ሽብሬን ለማሳተፍ አስቦ ነበር ነገር ግን አልቻለም፡፡ይህ ብቻ አይደለም/ድምጻቸውን በመቀየር ይቅርታ ይደረግልኝ ጌታነህ ይቅርታ ይደረግልኝ እልልታ ይቅርታ ይደረግልኝ ዶክተር/ ፊታቸውን በማዞር ልብሳቸውን አወላልቀው ወጣት ሆነው ይቀርባሉ/

**እልልታ**፡-/በድንገት ከተንበረከከችበት ተስፈንጥራ በመነሳት/ወንድም ዓለም ግርምዬ ነህ/ጭንቅላቱን በአዎንታ ሲያወዛውዝ ተጠምትማ  ትስመዋለች/

**ጌታነህ**፡-ምንድን ነው የማው ጋሽ አንዳርጌ ያንቺ ወንድም ናቸው፡፡ተዓምር ነው፡፡

**ግርማ**፡የወይዘሮ እልልታ ወንድም ነኝ፡፡ ለብዙ ዘመናት ተለያይተን ነበር፡፡ቤተሰባችን በዛሬው አቶ እሳቱ በትናንቱ አቶ አንበርብር የተበተነብን ምስኪን እህትና ወንድም ነን፡፡

**እልልታ**፡-አንበርብር?አንተ ሰይጣን የእናቴ ገዳይ የአባቴ ሞት ሰበብ፡፡

**ግርማ**፡-አዎን እልልታ ለአባታችን መሞት ሰበብ ለእናታችን መገደል ምክንያት የሆነ በስጋ ወደሙ በተጋቡ ባልና ሚስቶች ላይ የከፋት መርዙን የሚረጭ ዲያቢሎስ ያደረበት ፤ንብረት ዘርፎ የድሬደዋ ፖሊሶች ሊይዙት ሲሉ ተኩስ ከፍቶ ያመለጠው እና አንድ አይኑን በተኩሱ መሃል ያጣው  አንበርብር ይህ በመካከላችን የቆመው ስጋ ለበስ ሰይጣን እሳቱ ነው፡፡

**ሽብሬ**፡-ህልም አይምሰላችሁ እውን ነው፡፡የዚህ እኩይ ሰው ተግባር እናንተን በትኖ ሃብት ንብረታችሁን ወርሶ መኖር ነው፡፡ ለመሆኑ ጋሽ ጌታነህ ይህን እንዴት ልታምን ቻልክ፡፡

**ጌታነህ**፡-አንተ የጠፋኸው ባለቤቴ ወንድም ነህ፡፡ከሆንክስ እንዴት እዚህ በዘበኝነት ገባህ?ቤቱንስ እንዴት አወቅከው?

**ግርማ**፡-ከልጅነቴ ጀምሮ ከእህቴ ጋር ከተጠፋፋን በኋላቼ እኔ እናትና አባት ወደሌላቸው የህጻናት ማሰደጊያ ገብቼ ነበር፡፡ እዚያ ትምህርቴን ጨርሼ ስራ ይገኔ ነበር፡፡ነገር ግን እናትና አባቴ አሟሟት የእህቴም መጥፋት ሌት ከቀን እንቅልፍ ይነሳኝ ጀመር እናም ስራዬን ጥዬ እህቴን ለመፈለግና ይህን አረመኔ ለመከታተል ከድሬደዋ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ፡፡ ባጋጣሚ መንገድ ላይ አይቼው ተከታትዬው ስመጣ እዚህ ቤት ሲገባ  አየሁት፡፡ በተደጋጋሚ ስከታተለው እዚህ ቤት መምጣቱን ስላላቆመ እኔም እራሴን ለውጬ በዘበኝነት በመቀጠር እሱን ተከታትዬ ለማስያዝ  አቀድኩ፡፡ እናም በዘበኝነት ተቀጠርኩ፡፡ቤቱ ግን የእህቴ ቤት መሆኑን ያወቅኩት እልልታ ለዶክተር የእናትና አባታችንን መሞት የእኔን መጥፋት ስታጫውተው ሰምቼ ነው፡፡ይህን ለዶክተር ኢያጫወተችው በጣም አዝና ስለነበር ዶክተር ሀዘኗን እንድትተው እያጽናና ከተደፋችበት አቅፎ ሲያነሳት ይህ እኩይ ለመጥፎ ተግባር ተሰማርቶ ስለነበር ፎቶ ያነሳቸዋል

**እሳቱ**፡-/ከት ብሎ ይስቃል/ግሩም ቅንብር ድንቅ ተውኔት ነው የተጫወታችሁት እነሆ እፈራውና እጠላው የነበረውን የእስር ቤት ጫጫታና መከራ ገፈት ቀማሽ መሆኔ አይደል ጥሩ ነው አቶ ግርማ ጥሩ የወንጀል መርማሪ ፖሊስ ይወጣሃል ድንቅ ቅንብር ነው፡

**ግርማ**፡-አመሰግናለሁ

**እሳቱ**፡-ይቅርታ አድርጊልኝ ሽብሬ አንቺም መደነቅ አለብሽ በእኔ ላይ ቅዱስ የሆነ የበቀል ዱላ አሳረፍሽብኝ፡፡አንቺን እስከ እለተ ሞቴ አልረሳሽም፡፡ መጀመሪያ ያንቺን ቅዱስ በቀል በአጭር ጊዜ ውስጥ በእርኩስ በቀል እበቀለዋለሁ፡፡ከዚያ በፊት ግን/ከጎኑ ሽጉጥ አውጥቶ ይመታታል/ወደ ግርማ ሲያነጣጥር ጌታነህ ቀድሞ ጭንቅላቱ ላይ ደግንበታል/

**ጌታነህ**፡-እንዳትንቀሳቀስ እንዳትበላሽ ሽጉጥህን ጣል፡፡

**እሳቱ**፡-እሺ/ሽጉጡን ይጥላል እልልታ ለጥቂት ጊዜ ደንግጣ ፈዛ ከቆየች በኋላ መሀሉ ላይ እወደቀችው ሽብሬ ላይ ተደፍታ ታለቅሳለች//ግርማ ሽብሬን አንገቷን ደግፎ ይዞ ሊረዳት እየጣረ ዶክተርን ይጣራል/

**ግርማ**፡-እባክሽ ሽብሬ ጥቂት ጊዜ ታገሺ፡፡ሞት አይቅደምሽ የኔ እመቤት፡፡ዶክተር እባክህ እንደምንም ብለህ እርዳት፡፡ወይኔ እህቴ

**ዓለሙ**፡-/ትንሽ እንደመመርመር ብሎ/በፍጥነት መሄድ ከቻልን ሆስፒታል ድረስ መድረስ  ትችላለች በመኪና እንውሰዳት፡፡ /ሁለት ፖሊሶች ተከታትለው ይገባሉ እሳቱን እጁን በካቴና ይስሩታል/

**1ኛ ፖሊስ**፡-አንተ ምንድን ነህ ሽጉጡስ የምን ሽጉጥ ነው

**ጌታነህ**፡-ነፍሰ ገዳይ ነው፡፡ይቺን ምስኪን ገድሎ ሌላ ሊጨምር ሲል ነው የማረኩት፡፡

**1ኛ ፖሊስ**፡-አንሳው ጓድ /ሁለተኛው በመሀረብ ያነሳዋል/ ያንተስ ህጋዊ ነው፡፡

**ጌታነህ**፡-አዎን ጌታው ህጋዊ ነው/የፈቃድ ወረቀቱን ያሳየዋል/

**1ኛ ፖሊስ**፡-ለምን አንቡላንስ አይጠራም/ብሎ ሊደውል ሲል/

**ሽብሬ**፡-/ቀና ብላ ሆዷን ደግፋ እየተንገዳገደች /እ.....ያ.....ስ......ፈ....ል...ግ...ም.....እ.....ያ..........ስ.........ፈ.....ል.......ግ.......ም.....ዛሬ ይህ ቀን የደስታ ቀኔ ነው  በእኔ በአንዲቷ ኃጢአተኛ ደም የዚህ ቤት ሰይጣን ተመንግሎ ይወጣል፡፡እትዬ ፤ጋሼ ከዛሬ ጀምሮ አደራ እንዳትጣሉ ሰው በመካከላችሁ  አይግባ ለወሬኛ ጆሮ አትስጡ ሰይጣን ከመፈተን መቼም አይመለስም፡፡እኔንም ከፈተናው መስመር አስገብቶኝ ነበር፡፡እግዚአብሔር አምላክ ግን ጥሎ አልጣለኝም፡፡ህይወቴን አስተካከለልኝ፡፡ለዚች ለምትጠፋና ለምትከስም ዓለም ተገዢ እንዳለሆን አደረገኝ፡፡ደስ ይበላችሁ ከዚህ የበለጠ ድል አለ እንዴ ለዚያውም ቅዱስ ድል በሉ አሁን ነፍሴ በሰላም እንድታርፍ እያኳችሁ ተቃቀፉ፡፡ለኔ ብላችሁ በዚች በመጨረሻ ሠዓት የምለምናችሁን ልመናዬን ፈጽሙልኝ በሉ ተነሱ/ ሦስቱም ተነስተው ይተቃቀፋሉ/እሷም መሬት ላይ ትወድቃለች/

**መብራት ይጠፋል**

**ተፈፀመ** **ወስብሐት ለእግዚአብሔር!**